ዝናም ዘነመ፤ ጎርፍም ጎረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤
ያንን ቤት ገፉት፤ ነገር ግን አልወደቀም፤
በዐለት ላይ ተመሥርቷልና።
ማቴ ፯፥፳፭

# ስምዐ ጽድቅ



## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፭ ርእሰ አንቀጽ
፯ ሪፖርታዥ
፲፩ ቤተ አብርሃም
፲፬ ቃለ መጠይቅ
፲፰ የሕፃናት ዓምድ
፲፱ ትዝብት
፳፪ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ


## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በየወሩ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ


ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
Simatsidk12@gmail.com

ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል
የገጽ መልክእ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# በሮማኒያ በአክራሪዎች የተገደሉ ክርስቲያን ሰማዕታትን ለመዘከር የሕግ ማዕቀፍ ጸደቀ

በካሣሁን ለምለሙ



*በአክራሪዎች የተቃጠለ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን*

ክርስቲያኖች መብታችውን ተጠቅመው ያለምንም ስጋት አምልኮተ እግዚአብሔርን እንዲፈጽሙ የሰማዕታት ክረስቲያኖች መታሰቢያ ቀን እንደሚያግዝ ዘገባው አመልክቶ ቀኑን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በገንዘብና በሎጀስቲክስ ሊደግፉ እንደሚገባ ጠቁሟል፡፡ ነሐሴ ፯ ቀን በአክራሪዎች በግፍ የተገደሉ ክርስቲያን ሰማዕታትን ለመዘከር የተመረጠው በ፲፱፻፹፫ ዓ/ም የሮማኒያ ኦረቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በግፍ ሰመዕትነትን የተቀበሉበት ወቅት በመሆኑ ነው ተብሏል፡፡

በአክራሪዎች የተገደሉ ክርስቲያኖችን በየዓመቱ ለማሰብንና በዘመናችን በክርስቲያኖች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት በተመለከተ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚውል የሕግ ማዕቀፍ የሮማኒያው መሪ ካለሁስ ሎሃኒስ እንዳጸደቁ ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ዘግቧል፡፡

እንደ ዘገባው ከሆነ የሮማኒያው መሪ ካለሁስ ሎሃኒስ በዓመቱ ነሐሴ ፯ ቀን በአክራሪዎች የተገደሉ ክርስቲያኖች የሚታወሱበትና በዚህ ዘመን በክርሰቲያኖች ላይ እየተፈጸመ የለውን ጥቃት ለዓለም ሕዝብ በተለይም ለሮማኒያ ክረስቲያኖች ግንዛቤ መፍጠሪያ ቀን ሆኖ እንዲከበር ወስነዋል፡፡ ቀኑ ክርስትና ለዓለም ሕዝብ እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ ለወጣቶች ግንዛቤ ለመፈጠር እንደሚጠቅም ያነሳው ዘገባው አክራሪዎች በክርሰቲያኖች ላይ እፈጸሙ ያለውን ጥቃት መጠንና ዓይነት በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ለማስገንዘብም እንደሚያግዝም ዘገባው አመልክቷል፡፡

በዓለማችን በክርስቲያኖች ላይ ከፍተኛ የሆነ ሃይማኖታዊ ጥቃት የሚፈጸም ሲሆን ከሚፈጸሙት አጠቃላይ ሃይማኖት ተኮር ጥቃቶች ፹፭ በመቶ በክርሰቲኖች ብቻ እንደሚፈጸም ያስታወሰው ዘገባው በ፳፻፲፯ ዓ/ም በተለያዩ ድርጅቶች በተጠናው ጥናት መሠርት የተፈጸሙ ጥቃቶች ሁሉ የሚዲያ ሽፋን እንደተነፈጋቸው ተመላክቷል፡፡

አንድ ዓለም ዓቀፍ ደርጅት በ፳፻፳ዓ/ም ባጠናው ጥናት ደግሞ በክርስቲያኖች ላይ እየተፈጸመ ያለው ጥቃት አስከፊ ደርጃ ላይ መድረሱን ጠቁሟል፡፡ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከ፫፻፷ ሚሊዮን ክርስቲያኖች በላይ ከፍተኛ ለሆነ አካለዊና ሥነልቦናዊ ጥቃት እንደተጋለጡ ከዘገባው ለማወቅ ተችሏል፡፡

# የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ክርስቲያኖች አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ ጥሪ አቀረበ

## *ሲኖዶሱ የሃግያ ሶፊያን ቤተመቅደስ በተመለከተ መግለጫ አውጥቷል*

**በካሣሁን ለምለሙ**



*የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በስብሰባ ላይ*

የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ክርስቲያኖች ከመቼውም ጊዜ በላይ አንድነታቸውን ሊያጠናክሩ ይገባል በማለት መግለጫ እንዳወጣ ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ዘግቧል።

ቅዱስ ሲኖዶሱ በመላው ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያኖች ጥሪውን ያቀረበው የቱርክ መንግሥት ጥንታዊውንና ታሪካዊውን የክርስቲያኖች ቤተ መቅደስ የሆነውን ሃግያ ሶፊያን ከዘመናት በኋላ ወደ መስጅድነት መቀየሩን አስመልክቶ በተሰጠ መግለጫ እንደሆነ ዘገባው አመልክቷል።

የቱርክ መንግሥት የሃግያ ሶፊያን ይዞታ በመቀየር በይፋ ለሕዝበ ሙስሊሙ ማምለኪያነት እንዲሰጥ መወሰኑ ቅዱስ ሲኖዶሱን እንዳስቆጣ በመግለጫው ተመላክቶ የተወሰነው ውሳኔ የኦርቶዶክሳውያንን አብያተ ክርስቲያናት፣ የሀገራትን መንግሥታት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችንና የሰብአዊ መብት ተቋማትንና እንዲሁም የተለያዩ ሃይማኖት መሪዎችን ያላሳተፈ እንደነበረ የቅዱስ ሲኖዶስን መግለጫ ዋቢ አድርጎ የዘገበው ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ነው።

የቱርክ መንግሥት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የዓለም ክርስቲያኖችን ልብ የሰበረ ውሳኔ አሳልፏል ሲል ቅዱስ ሲኖዶሱ በመግለጫው እንዳነሳ ዘገባው ያመለከተ ሲሆን ውሳኔው የሃይማኖት እኩልነትን የላከበረና በቱርክም ሆነ በመላው ዓለም በሃይማኖቶች መካከል ሊኖር በሚችለው ትብብር ላይ ጫና ሊያሳድር እንደሚችልም ተዘግቧል።

በዓለማችን በተለይም በመካከኛው ምሥራቅ በርካታ ክርስቲያኖች በአክራሪዎች በግፍ በሚገደሉበት በዚህ ዘመን የቱርክ መንግሥት በሃግያ ሶፊያ ቤተ መቅደስ ላይ የወሰነው ውሳኔ በክርስቲያኖች ላይ ተጨማሪ ሕመምን ፈጥሯል ሲል ቅዱስ ሲኖዶሱ አስታውቋል።

ሃግያ ሶፊያ የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጥ የተገነባ ቤተ መቅደስ እንደሆነ ቅዱስ ሲኖዶሱ አስታውቆ በተለይ ለኦርቶዶክሳውያን ልዩ የሆነ ታሪካዊና መንፈሳዊ ጥቅም ያለው እንደሆነ አስገንዝቧል።

ውዱና በክርስቲያኖች ልብ ትልቅ ቦታ ያለውን ቤተ

መቅደስ ወደቀደመ ክብሩ ለመመለስ የቱርክ መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ሊያደርግ እንደሚችል ተስፋ እንዳለው የገለጠው ቅዱስ ሲኖዶሱ በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ቅዱስ ቦታው በቅርቡ ወደነበርበት ተመልሶ ለክርስቲያኖች አገልግሎት እንደሚውል ያለውን ተስፋ ገልጧል።

በዓለም በሚገኙ የተለያዩ ሃይማኖት ተቋማት መካከል ትብብርና መግባባት እንዲኖር የጠየቀው ቅዱስ ሲኖዶሱ ሃግያ ሶፊያ ወደቀደመ ክብሩ የመመለሱ ሂደት ለክርስቲያኖች ጊዜ የማይሰጠው ተግባር በመሆኑ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አስፈላጊውን ትብበርና ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርቧል።

ክርስቲያን ጠሎችና ዓለም በክርስቲያኖች ላይ እያደረሱ ያለውን ጫና ለመመከት ከምንጊዜ በላይ ሕዝበ ክርስቲያኑ አንድነቱን ሊያጠናክር እንደሚገባ ሲኖዶሱ አሳስቦ በዓለም የሚኙ አብያተ ክርስቲያናት ሰላምና ፍቅርን መመሪያቸው አድርገው በአንድነት በመቆም ችግሮችን በጥበብ ማለፍ እንደሚያስፈልግ ሲኖዶሱ ጥሪ አቅረቧል።



ወደ መስጂድነት የተቀየረው የሐጊያ ሶፊያ ቤተ መቅደስ

# በሶሪያ አዲስ የሐግያ ሶፊያ ቤተመቅደስ ሊገነባ ነው

በካሣሁን ለምለሙ



ፓትርያርክ ኪሪል እና የሶርያው ፕሬዝዳንት በሽር አላሳድ ሲወያዩ

በሩሲያ መንግሥት ድጋፍ በሶሪያ መለስተኛ የሆነ አዲስ የሐግያ ሶፊያ ቤተመቅደስ ሊገነባ እንደሆነ ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ዘግቧል።

ቤተመቅደሱ የሚገነባው በርካታ የግሪክ ኦርቶዶክሳውያን ሕዝበ ክርስቲያን በሚኖሩባት አል ሱቋአያላቢያህ ሲሆን ግንባታውም በቅርቡ ተጀምሮ በተያዘለት ጊዜ እንደሚጠናቀቅ ዘገባው አመልክቷል።

በቱርክ የሚገኘው ጥንታዊውና ታሪካዊው የሐግያ ሶፊያ ቤተመቅደስ ከርጅም ጊዜ በኋላ በቱርክ መንግሥት እምቢተኝነት የቤተመቅደሱ ይዞት በተወሰነ ደርጃ ተለውጦ በይፋ ወደ መስጅድነት ተቀይሮ ለሕዝበ ሙስሊሙ ማምለኪያነት እንደዋለም ዘገባው አስታውሷል።

# አጋጣሚዎችን በመጠቀም በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈጸም ጥቃት ይቁም!

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ መከራዎችን አሳልፋለች፡፡ በዚህም ከመገፋት ያረፈችበት፣ ከጥቃት የተረፈችበት ጊዜ የለም፡፡ እንዲያውም መገፋት ግብሯ እስከሚመስል ድረስ የመከራ ዶፍ የሚወድባት ግፍ ተቀባይና ተገፊ እየሆነች ነው፡፡ በየዘመናቱ አያሌ ፈተናዎችን ተሻግራ ዛሬ ላይ ብትደርስም አሁንም እንደጥንቱ ከውጪም ከውስጥም ብዙ መከራዎች እየተፈራረቁባት ይገኛሉ፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነት በሌላቸው ምክንያቶች ሁሉ በርካታ ጥቃቶች እየተፈጸሙባት ይገኛሉ፡፡ በእርግጥ መለያየትና መከፋፈል ከሌለ ህልውናቸው የሚያከትም የሚመስላቸው አካላት መከፋታቸውና ቤተ ክርስቲያንን በጠላትነት መፈረጃቸው የማይቀር ነው፡፡ ለዚህም ነው በሰበብ አስባቡ ቤተ ክርስቲያንን ማጥቃት ግብራቸው አድርገው የተያያዙት፡፡

ፖለቲከኞች እያራመዱት ያለው የዘውግ ፖለቲካና ርእዮተ ዓለም በታሪክ ስም በቤተ ክርስቲያን ላይ እየነዙት ያለው የሐሰት ትርክት ቤተ ክርስቲያንን በብዙኃኑ ዘንድ ጠላት አድርጎ በመፈረጅና ወዳጅ አልባ በማድረግ ለጥቃት እያመቻቿት ነው፡፡ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ሃይማኖታዊ አመክንዮ የሌላቸው በለውጥ ስም የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሁሉ የሚጠናቀቁት ቤተ ክርስቲያንን በማቃጠልና ኦርቶዶክሳውያንን በመግደል ሆኗል፡፡ ሐምሌ ፳፻፲ ዓ.ም በሶማሌ ክልል በክልሉ መንግሥት የተደራጀውና ሂጎ የተሰኘው ቡድን በታቀደና በተጠና መንገድ አብያተ ክርስቲያናትን አቃጠለ፤ ካህናትንና ምእመናንን በአሠቃቂ ሁኔታ በማረድ አስከሬናቸውን በእሳት አቃጠለ፤ ነፍሰ ጡርና ሕፃናትን ጨምሮ ብዙ ሴት ኦርቶዶክሳውያን ተደፈሩ፡፡ ቤታቸውን አስቀድሞ ቀለም በመቀባት በተቀናጀ መልኩ ሀብት ንብረታቸው በእሳት እንዲወድም አደረገ፡፡ በወቅቱ በጉዳዩ ላይ ሪፖርት ሲደረግ እንደነበረው የክልሉ ርእሰ መስተዳደር በነበረው ግለሰብ እና ግብረ አበሮቹ ላይ ክስ ቢመሠረትም ክስ ከተመሠረተባቸው በርካታ ተጠርጣሪዎች ውስጥ በቁጥጥር ሥር የዋሉ አሉ፡፡ ከደረሰውም ጥፋት አንጻር በአጥፊዎች ላይ የተወሰደው ርምጃ እዚህ ግባ የሚባል ባለመሆኑ ከዚያ በኋላ በተመሳሳይ መልኩ ጥፋት እያደረሱ ያሉ አካላትን ያበረታታ ይመስላል፡፡

በተመሳሳይ ሐምሌ ፳፻፲፩ ዓ.ም የሲዳማ ዞን ያቀረበውን የክልልነት ጥያቄ ተከትሎ ቀን ቆርጦ በተፈጸመ ጥቃት አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤ ኦርቶዶክሳውያን ተገድለዋል፡፡ ዞኑ የክልል ልሁን ጥያቄውን ማቅረብ ያለበት ለመንግሥት፣ መልስም መጠበቅ የነበረበት ከመንግሥት ሆኖ ሳለ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌላትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማጥቃት መነሻው ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ ከስምንት ያላነሰ አብያተ ክርስቲያናትን በማቃጠልና ኦርቶዶክሳውያን በመግደል ተጠርጥረው ክስ የተመሠረተባቸው ግለሰቦች ክሳቸው ተቋርጦ በነጻ ተሰናብተዋል፡፡

ከዚያም በኋላ ጥቅምት ፳፻፲፪ ዓ.ም መንግሥት ጥበቃዎቼን ሊያነሣብኝ ነው የሚል የአንድ ግለሰብን የተከብቤያለሁ ጩኸት ተከትሎ በተከፈተ ሃይማኖት ተኮር ጥቃት ንጹሐን ዜጎች ተገድለዋል፡፡ ከዚህ ቁጥር ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ኦርቶዶክሳውያን ሲሆኑ በተለይም በባሌ፣ በዶዶላ፣ በኮፈሌ፣ በምዕራብና ምሥራቅ

ሐረርጌ ብዙ ኦርቶዶክሳውያን ተገድለዋል፡፡ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ንብረታቸው ወድሞባቸዋል፡፡ በዚህ ጥፋት የተወሰደውን ርምጃ ስንመለከት ደግሞ ክስ ከተመሠረተባቸው ውስጥ የሚበዙት አጥፊዎች ሳይሆኑ ተጠቂዎች ነበሩ፡፡ ለማሳያ ያህል እነዚህን ጠቀስን እንጂ በተለያዩ አካባቢዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ተደራራቢ ጥቃቶች ሲፈጸሙ፣ በአጥፊዎችም ላይ ምንም ርምጃ ሳይወሰድ በአጸፋው ቤተ ክርስቲያን እንዳይቃጠልም ሆነ ራሳቸውን ከሞት ለማዳን የተከላከሉ ኦርቶዶክሳውያን እስርና እንግልት ሲፈጸምባቸው ታይቷል፡፡

**ዜጎች ሕይወት ሲያልፍ ከእነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ኦርቶዶክሳውያን ናቸው፡፡ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ በተለያዩ አካባቢዎች ኦርቶዶክሳውያን በሃይማኖታቸው ምክንያት ብዙ ግፍ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉ፣ ከቀያቸው የተፈናቀሉ ብዙ ናቸው፡፡**

በሰኔ ወር ፳፻፲፪ዓ.ም ደግሞ  በአዲስ አበባና በተለያዩ አካባቢዎች የጥፋት ኃይሎች በሰነዘሩት ጥቃት የንጹሐን ዜጎች ሕይወት ሲያልፍ ከእነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ኦርቶዶክሳውያን ናቸው፡፡ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ በተለያዩ አካባቢዎች ኦርቶዶክሳውያን በሃይማኖታቸው ምክንያት ብዙ ግፍ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉ፣ ከቀያቸው የተፈናቀሉ ብዙ ናቸው፡፡ ቤታቸውና ለብዙ ዓመታት በድካም ያፈሩት ሀብት ንብረታቸው እንዳልነበረ ሆኖ በእሳት ወድሞባቸዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የማንኛውም ሰው ሞት የማያስደስታት ብትሆንም በሞት ያጣችው የራሷ ልጅ ሆኖ ሳለ፣ በሐዘን ላይ ሐዘን ለመጨመር ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሌሎች ልጆቿንም በሞት አጥታለች፡፡

በአጠቃላይ ራሳቸውን ከሕግ በላይ ያደረጉ አካላት የሚያደራጁት ቡድን ጥቃት፣ የዞኖች የክልል እንሁን ጥያቄ፣ የዘውግ ፖለቲካ አራማጆች አቀባበል፣ የግለሰቦች የተከብቤያለሁ ጩኸትና የግለሰቦች ሞት ቤተ ክርስቲያንን ማጥቂያ መሣሪያ ሆነው አገልግለዋል፡፡ በእነዚህ ሁከቶች መሣሪያነት ቀድሞ የታሰበና የታቀደ በሚመስል መልኩ በቤተ ክርስቲያን ላይ ጥቃቶች ተፈጽመዋል፡፡ ከጥቃቱም በኋላ ጥፋት የፈጸሙ ወንጀለኞች ምንም ሳይደረጉ ሲቀሩና በተቃራኒው ተጠቂዎች ሲንገላቱና ሲታሰሩ ሲታይ ጥቃቱ መዋቅራዊና ስልታዊ ሆኖ የተፈጸመ ይመስላል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በሠራችው አገር፣ ባቀናቸው ቀዬ በሁሉ እየተገፋች ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ጥቃቶችና መገፋቶች ሕዝበ ክርስቲያኑን በአገሩ ተስፋ እንዲቆርጥ፣ የሚጠብቀው መንግሥት እንደሌለ በማሰብ ራሱን ለመጠበቅ ወደ መገደድ ጠርዝ እየገፉት ይገኛሉ፡፡ ይህ ቀቢጸ ተስፋ ደግሞ በአገር ላይ የማያባራ ግጭት ሊያመጣ የሚችል ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ጥቃቶች ከዚህ ወደ ከፋ ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት ጥቃት እያደረሱ ባሉ አካላት ላይ መንግሥት የማያዳግም ርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በተቃራኒ የጥቃቱ ሰለባ በሆነው ሕዝበ ክርስቲያን ላይ የሚደርሱ መገፋቶችና እንግልቶችም ሊቆሙ ይገባል፡፡

# አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እና መዘዙ

## በካሣሁን ለምለሙ

አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማለት የአንድ ሀገር መንግሥት ሕዝቡ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በሚገባበት ወቅት ዜጎች ማድረግና መደረግ የሌለባቸውን ጉዳዮች በዝርዝር የሚያስቀምጥ ሲሆን ዜጎች ማድረግ እያለባቸው ሳያደርጉ ሲቀሩ ወይም ማድረግ የሌለባቸውን ሲያደርጉ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

የአንድ ሀገር መንግሥት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ሊጥል የሚችለው ተፈጥሮአዊ አደጋ ሲከሰት፣ የእርስ በእርስ ግጭት ሲፈጠር፣ ረኀብና ድርቅ ሲከሰት እንዲሁም የማኅበረሰቡን ጤና የሚጎዳ ወረርሽ ሲከሰት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ታዲያ መንግሥታት እንደተፈጠረው ሁኔታ ዜጎቻቸው እንዲጠነቀቁና የሕይወት ዘይቤአቸውን እንዲቀይሩ ለማድረግ አስቸኳይ የሆነ አዋጅን ያውጃሉ፡፡ በዘመናችን አንዳንድ ሀገራት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተመሳሳይ መልኩ በዜጎቻቸው ላይ ገደብ ወይም አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲጥሉ ተስተውሏል፡፡ እነዚህ ሀገራት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከጣሉበት ምክንያት ከላይ ከተዘረዘሩት ችግሮች መካከል አንዱ በመከሰቱ ነው፡፡ ይኸውም የሰውን ልጅ ጤና የሚያውክ እና ለሞት የሚዳርግ ኮሮና ቫይረስ (COVID -19) የተባለ ወረርሽኝ በመከሰቱ ነው፡፡ ታድያ በዚህ ወረርሽኝ ምክንያት ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ የዓለማችን ሀገራት በዜጎቻቸው ላይ የተለያየ ገደብ በተለያየ ጊዜ ጥለዋል፡፡

ኮሮና ቫይረስ (COVID -19) የዓለምን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ያናጋ ሲሆን ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚህ ገፈት ቀማሽ በመሆኗ እንደሌሎች የዓለም ሀገራት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ካወጀች እነሆ ወራቶች ተቆጥረዋል፡፡ በኢትዮጵያ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከተጣለ ጊዜ ጀምሮ ታዲያ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ተስተጓጉለዋል፡፡ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከሌሎች እምነት ተቋማት በተለየ መልኩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ላይ እጅግ ውስብስብ የሆኑ ችግሮችን ፈጥሯል፡፡ አገልጋይ አባቶችን ለኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል፡፡ ቤተክርስቲያንም ከምእመናን ታገኝ የነበረውን የገንዘብና የቁስ ድጋፍ አስቀርቶባታል፡፡ ከእነዚህ ችግሮች በተጨማሪ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ቤተክርስቲያን በፀጥታ ችግር እንድትቸገርና የተደራጁ አክራሪ ቡድኖችንና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ሽፋን ያደረጉ አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች ምእመናንን ያለአግባብ እንዲደበድቡና በእስር እንዲያንገላቱ በር ከፍቶላቸዋል፡፡ መንግሥትና ሕዝብ ባለበት ሀገር ላይ አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች ለሚከተሉት ሃይማኖት ወግነው አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን እንደሽፋን ተጠቅመው ምእመናንን ይደበድባሉ፣ ያስራሉ አለፍ ሲልም በኢኮኖሚ ለማዳከም የብር መቀጮ ይጠይቃሉ፡፡

አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተጣለ ወዲህ በተለይ በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች የምእመናን መደብደብና የካህናት መታሰር የተለመደ ሆኗል፡፡ አንዳንድ የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ሕገ መንግሥቱን ተከትለው አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ማስፈጸም ሲገባቸው ነገር ግን የተጣለውን ገደብ እንደሽፋን በመጠቀም የግል ፍላጎታቸውንና ለሚከተሉት እምነት በመወገን ወቅቱን ተጠቅመው ቤተ ክርስትያንንና ምእመናን በከፍተኛ ሁኔታ እያጠቁ ያለፉበት እንደሆነ ከየአካባቢው እየወጡ ያሉ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት ምእመናን ከቤተክርስቲያን ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎት እያገኙ ስላልነበረ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር ባደረገችው ውይይት ምእመናን የመንግስትንና የጤና ባለሙያዎችን ምክር ተግባራዊ በማድረግ አገልግሎት እንዲያገኙ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በመሆኑም ምእመናን ክርስትና ማስነሳት፣ መቁረብና ማስቆረብ እንዲሁም በመጠኑም ቢሆን

ማስቀደስ ችለዋል፡፡ እነዚህ ሥርዓቶች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሞላ ጎደል ቢፈጸሙም በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ግን ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ትልቅ ችግር ገጥሟቸዋል፡፡

ምእመናንና አገልጋዮችን የፀጥታ ኃይሉ እንዳይተናኮልና እንዳያንገላታ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር የተስማማችውን ስምምነት የሚያስረዳ ግንቦት 5 ቀን 2012 ዓ.ም ባለ አምስት ገጽ ሸኚ ደብዳቤ ለየአህጉረ ስብከቱ ተልኮአል፡፡ አህጉረ ስብከቶችም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ የተወሰኑና በደብዳቤው ላይ የተቀመጡ ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስፈጸም ለየገዳማቱና አድባራቱ አሰራጭተዋል፡፡ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ውሳኔ ካሳለፈባቸው ነጥቦች መካከል "ምእመናን በአምልኮ ወቅት ርቀታቸውን እንዲጠብቁ፣ የጤና ባለሙያዎችን ምክር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲያደርጉ፣ ወርኀዊም ሆነ ዓመታዊ ክብረ በዓላት እንዲከበሩ፣ ካህናትንና ምእመናንን ያንገላቱ የፀጥታ ኃይሎች በሕግ እንዲጠየቁ እንዲሁም በየአብያተ ክርስቲያናቱ በር ላይ ያሉ የፀጥታ ኃይሎች እንዲነሱ" የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች ታዲያ በመንግሥት ታምኖባቸው ነው ቤተ ክርስቲያን መመሪያው እንዲተገበር ወደ የአጥቢያውና ገዳማቱ ያወረደችው፡፡ ነገር ግን በክብረ በዓላትም ሆነ ዘወትር የቤ ተክርስቲያን አገልግሎት ወቅት አብያተ ክርስቲያናቱ ከቅዱስ ሲኖዶስ የተላከላቸውን ሕጋዊ ደብዳቤ ቢያሳዩም ሕግን ተከትለው መስራት የማይፈልጉ አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች በአገልጋዮችና ምእመናን ላይ የሽብር ተግባር እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ የፀጥታ ኃይሎች ታዲያ ሕግና ደንብን ለማስከበር ሳይሆን ወቅቱን እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም የራሳቸውን ድብቅ ዓላማ ለመፈጸም መጓጓታቸውን የሚያሳይ ተግባር ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከፈተና የራቀች ባትሆንም አሁን እየደረሰባት ያለው ፈተና ግን የተለየ መልክ ተላብሶ ቀርቧል፡፡ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተጣለ ጀምሮ በቅርብ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን፣ በምእመናንና በአገልጋዮች ላይ  በየአካባቢው የተፈጸሙ ወንጀሎችን በዚህ ክፍል  የምንመለከት ይሆናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የምንመለከተው ለኦርቶዶክሳውያን የደም ምድር በመሆን የሚታወቀውን የጅማ ሀገረ ስብከት ይሆናል፡፡ ይህ ሀገረ ስብከት እንደሚታወቀው ክርስቲያኖች በጭካኔ የሚታረዱበት፣ የሚሰደዱበት እንዲሁም ሀብት ንብረታቸው የሚነጠቅበት አካባቢ ነው፡፡ በ09(9 ዓ.ም እንኳን በጅማ በሻሻ በሚባለው አካባቢ በአክራሪ ሙስሊም አማካይነት በርካታ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በጭካኔ በስለት ተቆራርጠው ሰማዕት እንደሆኑ ይታወሳል፡፡ የቅርብ ዓመታቱን ወንጀል ያየን እንደሆነ ደግሞ በዚሁ አክራሪ ሙስሊም አማካይነት "እምነታችሁን ቀይሩ" በማለት ኦርቶዶክሳውያኑን ገሚሱን ገድሎ ሌሎችን ደግሞ ለዘለዓለማዊ የአካል ጉዳት ዳርጓቸዋል፡፡

**ኮሮና ቫይረስ (COVID -19) የዓለምን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ያናጋ ሲሆን ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚህ ገፈት ቀማሽ በመሆኗ እንደሌሎች የዓለም ሀገራት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ካወጀች እነሆ ወራቶች ተቆጥረዋል፡፡**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በኦርቶዶክሳውያኑና በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰው ዘርፈ ብዙ ጥቃት መልኩን ቀይሮ ሕግን እናስከብራለን በሚሉ የፀጥታ ኃይሎች በኩል መከሠት ጀምሯል፡፡ በጅማ ሀገረ ስብከት የሚገኙ አንዳንድ

የፀጥታ ኃይሎች የተጣለውን አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንደ ሽፋን በመጠቀም በምእመናን ላይ በደል እየፈጸሙ ነው:: ይህ ድርጊት ታዲያ በአሁኑ ወቅት አልፎ አልፎ በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች የሚፈጸም ቢሆንም በጅማ ሀገረ ስብከት የሚፈጸመውን ያህል ግን የሆነ የለም:: ከሀገረ ስብከቱ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በቤተ ክርስቲያን፣ በምእመናንና በአገልጋዮች ላይ እየተፈጸመ ያለው ነውረኛ ድርጊት ለማንም የሚመኙት አይደለም::

በዚሁ በጅማ ሀገረ ስብከት በቅርቡ እንኳ ቅዱስ ሲኖዶስ የወሰነውን ውሳኔ ለየአድባራቱና ገዳማቱ ደብዳቤ በማሰራጨት ላይ የነበሩትን የሀገረ ስብከቱን ሥራ አስኪያጅ መልአከ ሰላም መምህር ተስፋ ሚካኤል አስፋን ያለምንም በደላቸው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ሽፋን በማድረግ አስሯቸው ነበር:: የሰኔ ሚካኤል የንግሥ በዓል በመከበር ላይ በነበርበት ወቅት እንዲሁ የጅማ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ የሆኑትን መልአከ ሣህል ቆምስ አባ ገብረ ኢየሱስን "በዓሉን ለምን ታከብራላችሁ" በሚል ሰበብ ታስረው እንደነበረ መረጃዎች ያመለክታሉ:: በተለይ በጅማ ከተማ ክርስቲያኖችን የሚያሳድዱና ቤተ ክርስቲያንን በክፉ ዐይን የሚመለከቱ አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች የደረጃ እድገት ተጠቃሚ እንደሆኑ ይነገራል:: ለአብነት ተጠቃሽ የሚሆነው ደግሞ የጅማው ሳጅን ጀማል ሐጂ ነው:: ከአካባቢው እንደተገኘው መረጃ ከሆነ ሳጅን ጀማል ሃጂ ክርስቲያኖችንና ቤተክርስቲያንን አምርሮ ከመጥላቱ የተነሳ "የእኛ ሰዎች ቤታቸው እየሰገዱ እናንተ ማናችሁና ቤተ ክርስቲያን ከፍታችሁ የምትጸልዩት" በማለት የግፍ ንግግር ይናገራል:: ያሻውን ያስራል፣ ያሻውንም ይፈታል:: ለሚከተለው ሃይማኖት ወግኖ ክርስቲያኖችን ያዋክባል፣ ያስራል::

የፀጥታ ኃይሎች በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ከፍተኛ ጥፋት ያደረሱ ሲሆን ምእመናንን ከማዋከብ፣ ከመደብደብ፣ ከማሰር ጀምሮ በኢኮኖሚ የደቀቁ እንዲሆኑ የብዙ ሺዎች ብር መቀጮ ይጥሉባቸዋል:: እስካሁን ባለው መርጃ መሠረት ከንምሳ ስምንት በላይ አገልጋዮችና ምዕመናን ታስረዋል:: ለእስር የበቁበት ምክንያት ደግሞ "አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ጥሳችኋል" የሚል ቢሆንም ነገሩ ግን ከዛ የዘለለ ነው:: ምእመናን አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አክብረው ሥርዓተ አምልኳቸውን በመፈጸማቸው ብቻ ይታሰራሉ ይደበደባሉ:: ክርስትና ሲያስነሳ ሲቆርብ ወይም ሲያቆርብ የተገኘ ደግሞ በሌለ ሀብቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ መቀጮ ይጠየቃል:: በዚህ ወቅት ከአንድ ሺህ ብር ጀምሮ እስከ አስራ አምስት ሺህ ብር የተቀጡ ምእመናን እንዳሉ መረዳት ተችሏል::

ይህንን እምነት ተኮር እንግልትና እስር የፈሩ በርካታ ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ከሚኖሩበት ጅማ አካባቢ እየተሰደዱ ይገኛሉ:: በተደራጁ አክራሪ ጽንፈኛ ቡድኖች ከሚደርሰው ጥቃት በዘለለ የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት ይጠብቃሉ ተብሎ ተስፋ ከሚጣልባቸው የፀጥታ አካል እንዲህ ዓይነት ዓይን ያወጣ የወንጀል ድርጊት ሲፈጸም ማየት በእርግጥም ያስደነግጣል:: የመንግሥት አንድ አካል ነኝ የሚለውና ሕግን ለማስከበር ዘብ ቆሚያለሁ የሚለው ሕግን ከጣሰ የተደራጀው ጽንፈኛ ቡድን ቤተ ክርስቲያንን ቢበድል፣ ክርስቲያኖችን ቢያርድና ቢያሳድ ምን ይፈረድበታል? "አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ" እንዲሉ በጅማና አካባቢው እየሆነ ያለው ነገር በጣም አሳሳቢ ነው::

በጅማ ሀገረ ስብከት እየተፈጸመ ያለው ዘርፈ ብዙ ጥቃት እጅግ ሰፊ በመሆኑ ሁኔታውን በጥቂቱ ለማሳወቅ አንኳር አንኳር ጉዳዮችን ብቻ ጠቅሰናል:: የጅማውን ጉዳይ እዚሁ ገታ እናድርግና ከጅማ ባልተናነሰ መልኩ ሌላው የኦርቶዶክሳውያን የመከራ ቀንበር ወደሚገኝበት ስልጤ ዞን እናቀናለን:: በስልጤ ዞን የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ምእመናን ከዚህ ቀደም የጭንቅና የመከራ ጊዜ ሲያሳልፉ እንደነበረ እናስታውሳለን:: የተደራጀ እስላማዊ አክራሪ ቡድን ወቅት እየጠበቀ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ከፍተኛ ጥቃት ይፈጽም እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው::

በዚሁ አካባቢ ሰሞኑን ሰኔ !1 ቀን !)02 ዓ.ም የእመቤታችንን ክብረ በዓል ለማክበር አዲስ አበባን ጨምሮ ከተለያየ አካባቢዎች ተሰባስበው በሄዱ ምእመናንና አገልጋዮች ላይ እንደተለመደው በአከባቢው የፖሊስ ኃይል አጋዥነት

የተደራጀ ጽንፈኛ ቡድን ከፍተኛ የሆነ ድብደባ ፈጽሟል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መገናኛ ብዙኃን ሰሞኑን ባወጣው ዘገባ መሠረት በስልጤ ዞን ቂልጦ አዝርነት በርበሬ ወረዳ በምትገኘው ሉዛ ቅድስት ማርያም ገዳም ክብረ በዓልን ለማክበር በሄዱ ምእመናን ላይ በተፈጸመ ድብደባ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን አስታውቋል። በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የነበሩ ምእመናንና አገልጋዮች ጥቃቱ የተፈጸመባቸው "አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ጥሳችሁ ተሰብስባችኋል" በሚል ቢሆንም እውነታው ሲገለጥ ግን ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው ለምን ተሰራ የሚል ሆኗል። በመሆኑም የአካባቢው የፀጥታ ኃይልም ሆነ የተደራጀው ጽንፈኛ ቡድን የምእመናንን በብዛት መሰባሰብንና አዲስ ቤተክርስቲያን መቋቋሙን የወደደው አይመስልም።

**እነዚህ በሞትና በሕይወት መካከል የተገኙ ምእመናንም በአቅራቢያ በሚገኝ የህክምና ተቋም የህክምና እርዳታ እንዲደረግላቸው ቢጠየቅም የትም መሄድ አይችሉም፤ ሁሉንም እዚሁ እንጨርሳቸዋለን የሚል ምላሽ ተሰጠ። በወቅቱ በቦታው ከፈጣሪ በታች ሊታደጋቸው የቻለ አንድም ምድራዊ ኃይል አልተገኘም።**

ለራሱ ሃይማኖት የወገነው የፀጥታ ኃይል በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሽፋን ምእመናንን በምሽት ከቅጥረ ቤተክርስቲያን ውጡ በማለት በሚያስገድድበት ወቅት ከሁለት መቶ በላይ የተደራጀ ጽንፈኛ ቡድን ድምጽ አልባ መሳሪያ ይዞ ውጭ ጥቃት ለማድረስ ይጠባበቅ ስለነበረ ምእመናኑም ወደ ውጭ አንወጣም የሚል ምላሽ ሰጡ። በአከባቢው የነበረው በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሽፋን የሚንቀሳቀሰው የፀጥታ ኃይልም የሕግ ከለላ እንደሚሰጣቸው ነግሯቸው ተስማምተው ወደ ውጭ ምእመናኑ በወጡበት ወቅት ውጭ ላይ ሥጋ እንዳየ ውሻ ይጠባበቅ የነበረው ጽንፈኛ አክራሪ ኃይል በታጠቀው ድምፅ አልባ መሳሪያ ምእመናንን ክፉኛ ደበደበ። ብዙ ምእመናንም በሞትና በሕይወት መካከል ተገኙ።

እነዚህ በሞትና በሕይወት መካከል የተገኙ ምእመናንም በአቅራቢያ በሚገኝ የህክምና ተቋም የህክምና እርዳታ እንዲደረግላቸው ቢጠየቅም የትም መሄድ አይችሉም፤ ሁሉንም እዚሁ እንጨርሳቸዋለን የሚል ምላሽ ተሰጠ። በወቅቱ በቦታው ከፈጣሪ በታች ሊታደጋቸው የቻለ አንድም ምድራዊ ኃይል አልተገኘም። አውጥቶ ለጅብ አሳልፎ የሰጣቸው ሕግ አስከባሪ መስሎ ሕግ ጣሽ የሆነው የፀጥታ ኃይልም ዳር ቆሞ በምእመናን ስቃይ ተደሰተ። ብዙዎቹ ምእመናን በጣም ጉዳት ስለደረሰባቸው ለተሻለ ህክምና ዘግይቶ በደረሰው የክልሉ ልዩ ኃይል ርዳታ ወደ አዲስ አበባ እንደተላኩም መረጃዎች ያሳያሉ። ቤተ ክርስቲያን አሁንም በየአቅጣጫው ጉዳቷ ቀጥሏል።

ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ምእመናን የጽንፈኞች መጫወቻ ከሆኑ ሰነባበተዋል። የተደራጁ አክራሪ ጽንፈኞች እንዳሻቸው ይፈነጩባቸዋል። የምእመናንን ሥቃይ የሚያስታግስ ስልታዊ በሆነ መንገድ የሚሰራ አካል እስካሁን ድረስ አልተገኘም። ጉዳዩ ባለቤት አጥቷል።

በየጊዜው የጉዳት ሰለባ የሚሆኑ ምእመናንም የሚመለከተው የመንግሥት አካልና የቤተ ክርስቲያን መሪ አባቶች አስቸኳይ መፍትሔ እንዲሰጡ ሁልጊዜ ይጠይቃሉ። ሀገር ባቆመች ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን ግፍና መከራ በኦርቶዶክሳዊ ቁመና በአንድነት ሕጋዊ መንገዶችን በመከተል የቤተ ክርስቲያንን ዘለቄታዊ መብትና ጥቅም ማስጠበቅ እንደሚያስፈልግ ምእመናኑ በየጊዜው ያሳስባሉ። እኔም እጅግ የከፋ የመከራ ዘመን እንዳይመጣ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ የጋራ ማድርጉ ይበጃል እላለሁ።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# የአብርሃም ቤት

*በቤተ ክርስቲያናችን ካሉት አሳሳቢ ችግሮቹ አንዱ ለመገናኛ በማይመቹ አካባቢዎች ያሉ በዕድሜ ብዛት እና በእንክብካቤ እጦት በመፈራረስ ላይ የሚገኙት፣ በውስጣቸው ብዙ ንዋያተ ቅድሳትንና ብርቅና ድንቅ ታሪካዊ ቅርሶችን የያዙት አብያተ ክርስቲያናት ችግር ነው:: ከዚህ አንጻር የዛሬው እንግዳችን አባ ዜና ገብርኤል ያደረጉት እንቅስቃሴ አበረታችና አስተማሪ በመሆኑ ከአባታችን ልንማር ይገባል በሚል የወሩ የ‹‹የአብርሃም ቤት›› እንግዳችን ሆነዋል:: አባ ዜና ገብርኤል የኖሩት በአዋሳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ነው:: ቤት ለእንግዳ…::*

አባ ዜና ገብርኤል እስከ ፲፱፻፶፰ ዓ.ም ድረስ በላስታ አውራጃ በዋልድቢት ማርያም ገዳም ይኖሩ ነበር:: ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ የጀመራቸው የሥጋ ደዌ በሽታ ስለተባባሰባቸው ለሕክምና ወደ ደሴ ከተማ መጥተው ከ፲፱፻፶፰-፲፱፻፷፫ ዓ.ም ቦሩ ሜዳ ሆስፒታል ሕክምናቸውን ሲከታተሉ ቆዩ:: ይህ ሕመም ሳይሻላቸውም ዓይናቸው ታመመ:: ከዚያም ለከፍተኛ ሕክምና ወደሻሸመኔ ኩየራ ሔዱ:: ሻሸመኔ ሲደርሱ ግን ሐኪሙ ወደሌላ ቦታ በመሔዳቸው ሳይታከሙ ቀሩ::

ከሻሸመኔ ወደ አገራቸው ለመመለስ የነበራቸው ገንዘብ በቂ አልነበረምና ሌላ መፍትሔ ያፈላልጉ ጀመር:: የታመመ ሐኪም መፈለጉን አይተውምና በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ‹‹ሐኪም አለ›› መባልን ሰመተው ወደአዋሳ ሄዱ:: ከአዋሳ ይርጋዓለም እየተመላለሱ ይታከሙ ጀመር:: መኖሪያቸውም በዚያው ሆነ:: በመጨረሻም ሕመሙ በከፍተኛ ሁኔታ በመባባሱ በ፲፱፻፷፭ ዓ.ም አዲስ አበባ አለርት ሆስፒታል ሁለት እግሮቻቸው ተቆረጡ:: የዚህ ታሪክ ባለቤት አባ ዜና ገብርኤል ይባላሉ::

አባ ዜና ገብርኤል አሁን እግሮቻቸውን፣ እጆቻቸውንና ዓይኖቻቸውን አጥተዋል:: የሚንቀሳቀሱትም በተሽከርካሪ ወንበር በሌላ ሰው እየተረዱ ነው:: ይህ ሁሉ ቢሆንም ግን ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አልተለዩም:: እጅ እግርና ዓይን ባይኖራቸውም እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ:: በዚህም በአዋሳ፣ በይርጋዓለምና በአካባቢው ወረዳዎች ምእመናንን በማስተባበር በየገጠሩ የሚገኙ የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናትን በመርዳት ላይ ናቸው:: አባ ዜና ገብርአል በሚያበረክቱት በዚህ አገልግሎት ለብዙ ጊዜ ተዘግተው የነበሩ፣ የንዋየተ ቅድሳት የዕጣን፣ የጧፍ፣ የመገበሪያ፣ የአልባሳት ወዘተ ከፍተኛ ችግር የነበረባቸው አብያተ ክርስቲያናት ተከፍተውና የሚያስፈልገው በመጠኑ ተሟልቶላቸው ለምእመናን አገልግሎት ለመስጠት በቅተዋል:: በተጨማሪም በእድሜ ብዛትና በእንክብካቤ ጉድለት የተጎዱ አብያተ ክርስቲያናትን በማስጠገን ላይ ናቸው:: በዚህ የተነሣ በአዋሳና በይርጋዓለም አካባቢ ምእመናን ዘንድ ከፍተኛ ፍቅርን አትርፈዋል:: ልጅ አዋቂ ሳይሉ በማስተባበር ሊስተካከሉ አይችሉም የብዙ አብያተ ክርስቲያናትን የንዋያተ ቅድሳትና የሌሎች ቁሳቁስ ችግር ለማቃለል ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው::

ዓይን የላቸውም ዓይን ያለንን ግን ይመሩናል፣ እጅ የላቸውም ያሠሩናል …

*ስምዐ ጽድቅ፡-* ስለትውልድዎ፤ ስለአስተዳደግዎና እስከአሁን ስላለው ታሪክዎ ቢገልጹልን?

*አባ ዜና ገብርኤል፡-* ሊጠቀስ የሚችል ብዙም ታሪክ የለኝም:: ብዙውንም ሥራ ራሴን ደብቄ በስውር ሳከናውን ነው የኖርኩት:: ስለዚህ እዚህ መጥቀሱ ተገቢ አይመስለኝም::

*ስምዐ ጽድቅ፡-* የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን መርዳት የጀመሩት መቼና እንዴት ነበር?

*አባ ዜና ገብርኤል፡-* /ከዚያ በፊት ያለውን ትተነው/ በ፲፱፻፸ ዓ.ም ሐምሌ ፲፫ ቀን ቤተ ክርስቲያን ቆሜ ጸሎት ሳደርስ አንዲት ሴት ተንበርክከው እያለቀሱ እመቤታችንን ይመጸኑ ነበር:: /ሴትየዋ ወ/ሮ ሙሉ እመቤት ይባላሉ:: በቅርቡም አርፈል/ በወቅቱ ወ/ሮ ሙሉ እመቤት ‹‹እንግዲህ መዘንጋቱን አንቺም ወደሽዋል…›› እያሉ ያለቅሱ ስለነበርና ስላሳዘኑኝም ጸሎታቸውን ሲጨርሱ ‹‹ምን ሆነው ነው?›› ብዬ ጠየቅኋቸው:: እርሳቸው

ከሚኖሩበት ከአለታወንዶ እየተመላለሱ የሚረዷትና ለፍልሰታም ለካህናትና ለመቀደሻ የሚያስፈልገውን ወጪ ሁሉ እየሸፈኑ የሚያገለግሏት ቤተ ክርስቲያን ካህን ጠፍቶ ለማስቀደስ እንዳልቻሉና ያሳዘናቸውም ይኸው እንደሆነ ነገሩኝ። ቀደም ሲል ቤተ ክርስቲያኒቱ በባላባቶች ተከባ በአካባቢውም ምእመናን እየተረዳች ትኖር ነበር፤ ከደርግ መምጣት በኋላ ግን ተከትሎ በመጣው ችግር ያለረዳት በችግር ኖራለች።

በዚህ መነሻነት በጣም አዝኜ በወቅቱ ወደነበሩት የወረዳው ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ሔጂ ጉዳዩን አስረዳኋቸው። እርሳቸውም ችግሩን ተረድተው ከሻሸመኔ ካህን እንዲመጣ አስደረጉልንና ያቺ ቤተ ክርስቲያን ፍልሰታን ተቀደሰባት። ወ/ሮ ሙሉ እመቤትን ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ በጠየቋቸው ጊዜ የዕጣን፣ የጧፍ፣ የአልባሳት፣ የመገበሪያና ሌሎችም ችግሮች እንዳሉ ነገርውኝ ስለነበረ ከዚያ ቀን ጀምሮ የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ የሚሰባሰበውን በየዓመቱ ለሴትዮዋ እየሰጠሁ፣ ካህናትንም ቀደም ብዬ በመፈለግና በማዘጋጀት ይህችን ቤተ ክርስቲያን በስውር ስረዳ ቆየሁ። እንግዲህ የመጀመሪያ መነሻ ይኼ ነው።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** *ይህ አገልግሎትዎ አሁን ወዳለበተ ደረጃ ያደገውስ እንዴት ነው?*

***አባ ዜና ገብርኤል፦*** በእርግጥ አሁን አገልግሎቱ አድጓል። በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ሄጄ እግሮቼ ተቆርጠው ወደ አዋሳ ከተመለስኩ በኋላ ልጆች ሊጠይቁኝ ይመጡ ነበር። ቤትም ጽዋ ይጠጡ ነበር። በዚህም መሠረት ግንቦት ፳፩ ቀን በነበረ ማኅበር ላይ አንድ መምህር ስለጽዮን ማርያም በሰፊው ካስተማረ በኋላ ገንዘብ አዋጥተን አክሱም ጽዮንን ብንረዳና ብንጎበኝ የሚል ሃሳብ አቀረበ።

በነገሩ ላይ ስንወያይም አክሱም ጽዮንን ሔዶ መሳለም በረክቷንም ማግኘት ተገቢ እንደሆነ ተነጋገረን። ከዚሁ ተጓዳኝ ግን በአቅራቢያችን በየገጠሩ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናትንም ማስታወስና መርዳት እንደሚገባ ተስማማን። ለዚህም ብዙ ቅርሳቅርስ የሚገኝባቸው፣ ታሪካዊ የሆኑ ነገር ግን የንዋየተ ቅድሳት፣ የዕጣን፣ ጧፍ እና ሌሎችም ችግሮች ያሉባቸው፣ በመፈራርስ ላይ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መኖራቸውን አስታውሼ የአቅማችንን እንርዳ የሚል ሐሳብ አቀረብኩ። ለመነሻ እንዲሆነንም የሲቄ ማርያም ቤተ ክርስቲያንን አስተዋወቅኋቸው። ሲቄ ማርያም በአለታ ወንዶ ወረዳ የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ነች።

በሐሳቡ በመስማማታችን በእኔ አስተባባሪነት ርዳታ ማሰባሰቡን ጀመርን። እኔ እንደ ድሮው ተዘዋውሬ ለመለመን ባልችልም ልጆቹ ያሰባሰቡትን ፳፻ ብር ሐምሌ መጨረሻ ላይ አምጥተው ሰጡኝ። እኔም ብሩን ለወ/ሮ ሙሉ እመቤት ሰጥቼ ልጆቹ ቦታዋን አይተው እንዲመጡ ላኳቸው።

**የስቄ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በጣም አሳዛኝ ነበር። በመንግጨት ለውጥ ጊዜ /፲፱፻፹፫/ በተፈጠረው ሁኔታ የመቃብር ቤቶቹ ቆርቆሮ ሳይቀር እየተነቀሉ ተወስደዋል። ደጀ ሰላሙም ፈራርሷል። ቤተ ክርስቲያኒቱ አጥር ስለሌላትም ከብቶች የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ እየታከኩ አፈራርሰውታል።**

የስቄ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በጣም አሳዛኝ ነበር። በመንግጨት ለውጥ ጊዜ /፲፱፻፹፫/ በተፈጠረው ሁኔታ የመቃብር ቤቶቹ ቆርቆሮ ሳይቀር እየተነቀሉ ተወስደዋል። ደጀ ሰላሙም ፈራርሷል። ቤተ ክርስቲያኒቱ አጥር

ስለሌላትም ከብቶች የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ እየታከኩ አፈራርሰውታል። ይህ ሁሉ ያዩት ልጆች በየወሩ መዋጮ ለማዋጣትና የሲቄ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ሌሎች የገጠር አብያተ ቤተ ክርስቲያናትንም ለመርዳት ወሰኑ። ሥራውን የማስተባብረውም እኔ ነበርኩ።

በዚህም መሠረት መስከረም ፳፩/፲፱፻፹፯ ዓ.ም በአሥራ ዘጠኝ ፈቃደኛ ሰዎች በተጀመረው እንቅስቃሴ በዚያው ዓመት የሲቄ ማርያም ቤተ ክርስቲያንን አጥር አሳጥረን፣ የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃ ግድግዳና ደጀ ሰላም አጠናክረን አሠራን። አሸዋ ከይርጋዓለም በማስመጣት ወለሉንና ግድግዳውን በሚገባ ለማሠራት ቻልን። ከዚህ በኋላ አገልግሎቱ እየሰፋ፣ የሚሳተፉትም ምእመናን ብዛት እየጨመረ ሔደ።

*ስምዐ ጽድቅ፡-* ምእመናንን ሲያስተባብሩ ዋና ዓላማዎ ምን ነበር?

አባ ዜና ገብርኤል፡- ዋና ዓላማችን ከመገናኛ እጥረት ከቦታ ርቅት የተነሣ ረዳት ያጡ አብያተ ክርስቲያናትን መርዳት ነው። በተለይ ከ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ጀምሮ የአካባቢያቸው ሰዎች በመፈናቀላቸው ለከፍተኛ ችግር የተዳረጉ፣ ዙሪያቸውን በመናፍቃን የተከበቡ፣ ተንከባካቢ አጥተው በመፈራረስ ላይ ያሉ ብዙ ቅርሶችን የያዙ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ጥቂት አይደለም። ስለዚህም ሁላችንም ባለብን የሃይማኖት ግዴታ መሠረት ያለፍላጎታቸው ወደመናፍቃን የሚፈልሱትን ምእመናን ለመመለስና በተያዩ ችግሮች የተነሣ ሳይቀደስባቸው የሚቆዩ አብያተ ክርስቲያናትን ለመርዳትና ባሉበት ለማጠናከር አቅማችን የፈቀደውን እየረዳን ነው። በአጠቃላይ ምእመናንን በማሰባሰብ ሰባኪ መድቦ ወንጌል እየተሰበከላቸው፤ ቅዳሴ እየተቀደሰላቸው በንስሓ እየተመለሱ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ማድረግ ነው ዓላማችን።

*ስምዐ ጽድቅ፡-* በእርስዎ አስተባባሪነት የረዷቸውን አብያተ ክርስቲያናት ጥቂቱን ቢጠቅሱልን?

*አባ ዜና ገብርኤል፡-* ብዙ ናቸው። የማስታውሳቸውን ብቻ ልንገርህ። የመጀመሪያዋ የሲቄ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ነች። በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም የተሠራው የዳንዴ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛው ነው። ሌላው የአቡነ ኤውስጣቴዎስ ቤተ ክርስቲያን ነው። በሸበዲኖ አካባቢ ከአረንጃ መድኃኔዓለም ቀጥሎ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የተሠራ ነው። በሀገረ ሰላም የሚገኘው ታሪካዊውን የሁርሶ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳምም እየረዳን ነው። ከአዋሳ ብዙም የማይርቀው ሌላው ቤተ ክርስቲያን የጻድቁ የገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ነው። በሸበዲኖ ወረዳ ወንዶ ጢቃ አካባቢ የሚገኘውን የጋንጌሶ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንም በመርዳት ላይ ነን።

*ስምዐ ጽድቅ፡-* አካል ጉዳተኝነትዎ በአገልግሎትዎ ላይ የፈጠረብዎት ችግር አለ?

*አባ ዜና ገብርኤል፡-* እውነት ለመናገር አካል ጉዳተኝነቴ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ብዙም ችግር አልፈጠረብኝም። ምክንያቱም ወንድሞቼና እኅቶቼ ልጆቼ ሳይጸየፉና ሳይከሩ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ያደርጉልኛልና ነው። መሔድ በምፈልግበት ጊዜ እየተሸከሙ ወደመኪናዬ በማውጣትና በማውረድ በመሳሰሉት ይደግፉኛል።

*ስምዐ ጽድቅ፡-* ለምእመናን የሚያስተላልፉት መልእክት አለ?

*አባ ዜና ገብርኤል፡-* አዎ ማለት የምፈልገው ነገር አለ። ምእመናን የሚደነቁትንና በብዛት የሚታወቁትን ብቻ ሳይሆን በየገጠሩ የሚገኙትን ብዙ ቅርሶችን የያዙትንና በመፈራረስ ላይ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ሊያስታውሱ ይገባል። በተለይ ወጣቶች በየገጠሩ ለመናፍቅነትና ለሱስ የተዳረጉትን ወንድሞቻችን ፈልግ ተከትሎ በየገጠሩ ማስተማርም ይገባል። ዛሬ ብርቅና ድንቅ የምንላቸውን አብያተ ክርስቲያናት አባቶቻችን ባይጠብቁልን ኖሮ አናያቸውም ነበር። ስለዚህ እኛም ለተተኪው ትውልድ የምናወርሰው እንዳናጣ መትጋት ይኖርብናል።

# ''ጥቃትን ለመከላከል የምናደርገው ጥረት አናሳ በመሆኑ ጉዳቱ ተዳፍኖ ይቀራል''

በካሣሁን ለምለሙ

የተከበራችሁ አንባብያን ‹‹ቃለ መጠይቅ›› በጋዜጣችን አምዶች ላይ በአደረግነው የአምዶች ማሻሻያ መሠረት ቃለ መጠይቅ የሚል አዲስ አምድ ይዘንላችሁ ቀርበናል:: በዚህ አምድም በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ቃለ መጠይቃዊ ቆይታዎችን እናደርጋለን:: በመሆኑም በዚህ እትማችን ወቅታዊ የሆነውን የቤተክርስቲያንና የምእመናንን ጥቃት በተመለከተ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የሕግ አገልግሎት መምሪያ ዋና ኃላፊ ከሆኑት ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ሽመልስ ቸርነት ጋረ ያደረግነውን ቆይታ ይዘንላችው ቀርበናል:: ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ሽመልስ ቸርነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባሉ አህጉረ ስብከት በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፎች ለረዥም ጊዜ ሲያገለግሉ የቆዩ አባት ናቸው::

ከሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ጀምሮ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ዋና ዋና የአገልግሎት ክፍሎች ሲያገለግሉም ቆይተዋል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕግ አገልግሎት መምሪያ ዋና ኃላፊ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ:: ዝግጅት ክፍላችንም በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ላይ በተደጋጋሚ እየተፈጸመ ያለውን ጥቃት እና የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ለመከላከል በተጣለው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በተመለከተ ጉዳዩ ከሕግ አንጻር እንዴት ይታያል? በሚልና የሕግ አገልግሎት ማስተባበሪያው ምን እየሠራ እንደሆነ ለመቃኘት ከዋና ሥራ አስኪያጁ ጋር ያደርግነውን ቆይታ ይዘንላችሁ ቀርበናል:: መልካም ንባብ::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** የኮሮና ቫይረስ ወረርኝን ለመግታት በተላለፈው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የሕግ አገልግሎት መምሪያው ምን ምን ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል?

***ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ሽመልስ ቸርነት፡-*** የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በሀገራችን መከሠቱን መንግሥት ካረጋገጠበት ጊዜ አንሥቶ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁ ይታወቃል:: መንግሥት ይህንን ያደረገው የዜጎችን ጤንነትና ሰላም ለመጠበቅ በማሰብ ያስቀመጠው አዋጅ መሆኑን እንረዳለን:: የበሽታውን መስፋፋት መግታት የመንግሥት ተግባር ብቻ ባለመሆኑ ቤተ ክርስቲያንም ትልቅ ድርሻ እንዳለባት ስለሚታወቅ የድርሻዋን እየተወጣች ትገኛለች:: ቅዱስ ሲኖዶስም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ የኮሮና በሽታ ሥርጭትን መከላከል ላይ ትኩረቱን ያደረገ ግብረ ኃይል አቋቁሞ እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመረ ወራቶች ተቆጥረዋል:: የተቋቋመው ግብረኃይል ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተል ሲሆን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት መንበረ ፓተርያርክ ጀምሮ እስከ ታች ሀገረ ስብከት ደረጃ መዋቅር ተዘርግቷል:: እስከ አጥቢያ ድረስ መዋቅሩ የሚሠራ ሲሆን ሕዝበ ክርስቲያኑም እራሱንና ቤተሰቡን ከመጣው ወረርሽኝ እንዲጠበቅ በግብረ ኃይሉ አማካይነት መመሪያዎች ይተላለፋሉ:: የሕግ አገልግሎት መምሪያውም ከተቋቋመው ግብረኃይል ጋር በመቀናጀት የወረርሽውን መከላከል ሥራውንም ሆነ የሕግ አገልግሎት ደጋፍ እየሰጠ ይገኛል::

***ስምዐጽድቅ፡-*** የኮሮና ወረርሽኝን ለመከላከል የተጣለውን

አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሽፋን በማድረግ አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች በአንዳንድ አካባቢዎች በቤተ ክርስቲያን፣ በምእመናንና በአገልጋዮች ላይ ከፍተኛ ጥቃት እየፈጸሙ እንደሆነ መርጃዎች እየወጡነውና በዚህ ላይ የሕግ አገልግሎት መምሪያው ምን እየሠራ ነው?

***ሊቀትጉሃን ቀሲስ ሽመልስ፡-*** አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ለሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል እኩል እንዲያገለግል ተብሎ በመንግስት ታምኖበት የተጣለ ነው። የሚጠቅም ከሆነ ሁሉን የሚጠቅም ይሆናል የሚጎዳ ከሆነ ደግሞ ሁሉንም የሚጎዳ ይሆናል ማለት ነው። አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተጣለ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ውስብስብ በሆነ ፈተና ውስጥ ትገኛለች። በመሆኑም ከኢኮኖሚ ጉዳት ጀምሮ ልዩ ልዩ የፀጥታ ችግሮችም ተከስተውባታል። አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን እንደ ሽፋን በመጠቀም በቤተ ክርስቲያንና በምዕመናን ላይ ከፍተኛ የሆነ የፀጥታ ችግር እየፈጠሩ ያሉ አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች እንዳሉ ከምእመናን አንደበት እንሰማለን። ነገር ግን አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በተመለከተ ከሕግ አገልግሎት ማሥተባበሪያው ይልቅ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ የተቋቋመው ተስፋ ቡድን ግብረ ኃይል የሚመለከተው ሲሆን የሕግ አገልግሎት መምሪያውም ሕግና ሕግ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ድጋፊ ያደርጋል።

የተቋቋመው ተስፋ ግብረኃይል በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት በቤተክርስቲያንና በምእመናን ላይ ለሚከሰት ማንኛውም ችግር በዋናነት ምላሽ ይሰጣል፤ ጉዳዩን ይተነትናል፤ ግምገማም ያካሄዳል። የሕግ አገልግሎት ማስተባበሪያው ግብረ ኃይሉ ከሚከተለው እውናዊ ሂደት ባሻገር በአንዳንድ አካባቢዎች አስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ሽፋን አድርገው አንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች በቤተ ክርስቲያንና በምዕመናን ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥፋትና በደል እያደረሱ መሆኑን የሚያሳዩ ተጨባጭ መረጃዎች እስካሁን አልቀረቡም።ነገር ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ችግሮች እየተፈጠሩ እንደሆነ ከምእመናንም ሆነ ከማኅበራዊ ትስስር ገጽ እንመለከታለን።

እየተፈጸሙ ያሉ የወንጀል ድርጊቶች በማስረጃ ተደራጅተው ቢቀርቡም ከግብረ ኃይሉ ቀድሞ ጉዳዩን ማየትና መከላከል ያለበት ችግሩ የተፈጠረበት ሀገረ ስብከት ነው። ምክንያቱም በሀገረ ስብከቱ ሥር በሚገኙ ምእመናንም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ላይ ችግር ሲከሰት ቅድሚያ የሚጠየቀው ሀገረ ስብከቱ ነው።

እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ወንጀልን የሚከላከልበት የሕግ መዋቅር አለው። በዚህ የሕግ መዋቅር ተጠቅሞ የወንጀል መከላከሉን ሥራ ሊሠራ ይገባል። ከዚህ ውጭ ግን አህጉረ ስብከት የወንጀል መከላከሉ ሥራ አቅማቸው በላይ ሲሆንና የጠቅላይ ቤተ ክህነትን የሕግ አገልግሎት መምሪያ እገዛ በሚጠይቁበት ወቅት መምሪያው ጉዳዩን በበላይነት ይዞ ለመፋታትና በሕግ አግባብ እንዲዳኝ ጥረት ያደርጋል። በመሆኑም በአንዳንድ አካባቢዎች በአንዳንድ የፀጥታ ኃይሎች እየተፈፀመ ያለው የወንጀል ድርጊትም በዚህ አግባብ ሊዳኝ ይገባዋል። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ "እገባለሁ አትገባም" በሚል ውዝግብ ውስጥ የራሳቸውን ዓላማ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የሚጣደፉ የፀጥታ ኃይሎች እንዲሉ ተደርጓል። በመሆኑም ጉዳዩን በትዕግሥትና በጸሎት ከማለፍ በዘለለ በሕግ አግባብ የሚጠየቁበትን ሁኔታ በማመቻቸት ብቻ ችግሩን ለማለፍ መሞከር ተገቢ ነው። በዚህ ረገድም የተቋቋመው የተስፋ ግብረ ኃይል ወንጀሎችን የመከላከል ሥራ ይሠራል። ጉዳዩ ከአቅም በላይ የሚሆንም ከሆነ የሕግ ሰንሰለቱን ጠብቆ ፍትሕን የሚያስገኝ ይሆናል።

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** አንዳንድ ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወሰኑ ውሳኔዎች የተፈጻሚነት ችግር እንዳለባቸው ይነገራልና የሕግ አገልግሎት መምሪያው ይህንን ጉዳይ እንዴት ይመለከተዋል?

***ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ሽመልስ፡-*** የሕግ አገልግሎት መምሪያው የተቋቋመበት ዋና ዓላማ ወንጀልን መከላከልና ፍትሕን ማስፈን ነው። የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶችን ትኩርት ሰጥቶ ወደ ፍትሕ አካላት የመውሰድ ሥራን ይሠራል። የወንጀል ሕጉ ዓላማም አጥፊ እንዲቀጣ ለወደፊቱም ተደራራቢ የወንጀል ድርጊት እንዳይፈጸም ማስተማር

ነው። በተጨማሪም የወንጀል ድርጊቱን ቅጣት ያዩ ሌሎች ለወንጀል ድርጊት እንዳይነሣሡ ለማድረግ ነው።

እንደሚታወቀው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለየ መልኩ በቤተ ክርስቲያን መዋቅር በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ከፍተኛ የሆነ የተቀናጀ ጥቃት ሲፈጸም እናያለን። በመሆኑም በእነዚህ መሰል የወንጀል ድርጊቶች ቅዱስ ሲኖዶስ በተደጋጋሚ የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ወንጀሎችን ሁሉ የሕግ አገልግሎት መምሪያው ብቻውን መወጣት ስላልቻለ ቅዱስ ሲኖዶስ በሕግ አገልግሎት ሥራ ላይ የተሠማሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሕግ አገልግሎት መምሪያውን እንዲያግዙ ለማድረግ ታቅዷል። ለአብነትም ራሱን ‹‹የኦሮሚያ ቤተ ክህነት አደራጅ›› ብሎ የሚጠራው የተደራጀ ቡድን በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን በመቅረብ በቤተክርስቲያን ላይ የስም ማጥፋት ሥራ እየሠራና በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ የሆነ ዘርፈ ብዙ ጥቃት እየፈጸመ ይገኛል። በመሆኑም ከዚህ በኋላ የሕግ አገልግሎት መምሪያም ሆነ በሕግ አገልግሎት የተሠማሩ የቤተ ክርስቲያኗ ልጆች የግለሰቦችን ሁኔታና የወንጀል አፈጻጸም ሂደትን በመቃኘት ወንጀለኞችን ወደ ሕግ የማቅረብ ሥራ ይሠራሉ። ይህንን ለማስፈጸምም ከሕግ ባለሙያዎች ጋር ውይይት እያደረግን እንገኛለን።

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የወንጀል መከላከል ሥራውን ከምንጊዜም በላይ ተጨባጭ ለማድረግ የቤተ ክርስቲያን የሕግ አገልግሎት መምሪያው ከማኅበረ ቅዱሳን የሕግ አገልግሎት ክፍልና ከተለያዩ የሕግ አገልግሎት ከሚሰጡና ቤተ ክርስቲያን ከመረጠቻቸው አካላት ጋር እየሠራን ነው። የጋራ እቅድ አውጥተን ቤተ ክርስቲያን ይህ ሁሉ መከራ እየወረደባት ባለችበት ወቅት ‹‹በመንቀሳቀስ ላይ ነን›› መባሉ ተገቢ አይደለም።

ከዚህ ቀድሞ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በምእመናን ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ሁሉ ክትትል ተደርጎባቸው የሕግ አፈጻጸሙ ለሕዝበ ክርስቲያን ይፋ ይሆናል። እስከዚያ ድረስ ግን እያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት ክትትል እየተደረገበት እንደሆነ ለመግለጽ እወዳለሁ።

*ስምዐ ጽድቅ፡-* በአዲስ አበባና በሌሎች አንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች ሆን ተብሎ ርቀታቸውን ያልጠበቁ መስጂዶች እየተሠሩ ይገኛሉ። በዚህ ደረጃ የሕግ አገልግሎት ማስተባበሪያው ምን ይላል?

*ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ሽመልስ፡-* የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር በደንብ መረዳት መሰል የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ያግዘናል። ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ጀምሮ እስከ አጥቢያ ድረስ ያለው አደረጃጀት ሀብትን የመጠበቅ፣ ወንጀልን የመከላከል፤ አገልግሎትን የመፈጸምና ግዴታን የመወጣት አብሮ የተሰጡ ሥልጣኖችንና መብቶች ናቸው። ርቀታቸውን የጠበቁ የአምልኮ ቦታዎች ተመሥርተው አምልኮን መፈጸም እየተቻለ ሆን ተብሎ ሃይማኖታዊ ግጭትን ለመቀስቀስ ርቀታቸውን ያልጠበቁ የአምልኮ ቦታዎች በተለያየ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተሠሩ እንደሆነ በተለያየ መንገድ ቅሬታዎች እየመጡ ይገኛሉ። ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት የሀገሪቱን የመሬት ማኔጅመንት ፖሊሲ ማየት ይጠይቃል። ርቀታቸውን ያልጠበቁ የአምልኮ ቦታዎች መሠራታቸው ለሁለቱም ቤተ እምነቶች ከትንኮሳ ውጪ ሰላምን አያመጡምና የመንግሥትን የመሬት አስተዳደር ፖሊሲን መመልከት መልስ ይሆናል።

አንድ የአምልኮ ተቋም ከሌላው የአምልኮ ተቋም በምን ያህል ርቀት ሊቋቋም ይገባዋል? የሚለውን መመሪያ በመመልከት መንግሥትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ዘላቂ መፍትሔ ሊሰጡ ይገባል። በቅርቡ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አፍሪካ ኅብረት አካባቢ እንደዚህ ዓይነት ችግር ተከሥቷል። ይህንን ችግር ለመፍታት የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ባለው የሕግ አደረጃጀት ጉዳዩን ሊከታተል ይገባዋል። ከሀገረ ስብከቱ አቅም በላይ ከሆነ ደግሞ በሚጠይቀው ጥያቄ መሠረት የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሕግ አገልግሎት መምሪያ ጣልቃ በመግባት ሕጋዊ ድጋፍ የሚያደርግ ይሆናል። ስለዚህ እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት በራሱ አደረጃጀት አማካይነት የቤተ ክርስቲያንን መብትና ክብር ያስጠብቃል፤ ከአቅሙ በላይ ከሆነ ደግሞ የእኛ መምሪያ ድጋፍ ያደርጋል ማለት ነው፡

ከዚህ ውጭ አህጉረ ስብከቶች ሥልጣኑና ኃላፊነቱ ተሰጥቷቸው እያለ በቤተ ክርስቲያኗ ላይ የሚከሠቱ ችግሮችን በቸልተኝነት የሚያልፉ ከሆነ የማትጋት የመቀስቀስና ጣልቃ የመግባት ሥራን እንሠራለን።

*ስምዐ ጽድቅ፡-* ዘላቂ የቤተ ክርስቲያንን ጥቅምና መብት ለማስከበር ምን እየተሠራ ነው? ለወደፊቱስ ምን ታስቧል?

*ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ሽመልስ፡-* የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት ማስጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባራችን ሊሆን ይገባል። በዚህ ረገድ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ ሪፖርቶችን እያዘጋጀን እንገኛለን። በቀጣይ ፳፻፲፫ ዓ.ም በጀት ዓመት ዋናውና ቅድሚያ ልንሰጠው ያሰብነው ተግባር ይህንኑ ነው። ተፈጻሚነቱም በሂደት የሚይታይ ይሆናል። በሕግ ፊት ምን ማለት ነው። ጉዳይና ወንጀልን የመከላከል ጉዳይ እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት በተሰጠው ኃለፊነት የወንጀል መከላከል ሥራዎች ይሠራሉ።

**በወንጀል መከላከል ሥራ ላይ ለእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። የወንጀል ድርጊት መከላከል የቤት ሥራዎችን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊከፋፍሉ ይገባል። ካልሆነ ግን በአንድ የሕግ አገልግሎት መምሪያ ብቻ ሥራዎችን መሥራት አይቻልም።**

በወንጀል መከላከል ሥራ ላይ ለእያንዳንዱ ሀገረ ስብከት ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። የወንጀል ድርጊት መከላከል የቤት ሥራዎችን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊከፋፍሉ ይገባል። ካልሆነ ግን በአንድ የሕግ አገልግሎት መምሪያ ብቻ ሥራዎችን መሥራት አይቻልም። አህጉረ ስብከትም በወንጀል መከላከል ዙሪያ እርስ በርእሳቸው ልምድ የመለዋወጫ መድረኮችን ሊያዘጋጁ ይገባል። የወንጀል መከላከል አቅም ሲፈጠር በየጠረፉ የሚከሠቱ ወንጀሎችን የመቆጣጠር ብቃት ያድጋል። ወንጀልን ለመከላከል ሁልጊዜ ንቁ ሆኖ አቅም ፈጥሮና ተዘጋጅቶ መገኘት ያስፈልጋል። የፋይናንስና የሰው ኃይል አደረጃጀቱንም የተስተካከለ ማድርግ ያስፈልጋል።

*ስምዐ ጽድቅ፡-* ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?

*ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ሽመልስ፡-* ቤተ ክርስቲያናችን በሕግና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥታ የሠራችበት ጊዜ የለም። በመሆኑም በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ጥቃት ሲፈጸም የሁሉንም ስሜት ጎድቶት ያልፋል። ያንን ጥቃት ለመከላከል የምናደርገው ጥረት አናሳ በመሆኑ ጉዳዩ ተዳፍኖና የኋላ ታሪክ ሆኖ ይቀራል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ አዲስ የወንጀል ድርጊት ይፈጸማል። አሁንም ጉዳዩ መፍትሔ ሳያገኝ ሁሌም የተዳፈነ እሳት ሆኖ ይቀራል። ስለሆነም ጉልበት ያለው በጉልበቱ፤ ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፤ እውቀት ያለው በእውቀቱ እንዲሁም ሀሳብ ያለው በሀሳቡ በወንጀል መከላከሉ ሥራ ላይ ቤተ ክርስቲያኗን ሊያግዛት ይገባል። ከዚህ በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያኗን የተረዳ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ሥቃይ ሊያሳስበው የሚችል ማኅበረሰብ አቀፉ ግብረ ኃይል በማቋቋም የቤተ ክርስቲያንን ክብር ለማስጠበቅ ትኩረት ሰጥቶ ከመሥራቱ በዘለለ የወንጀል መከላከል ስልታችን ምን መምሰል አለበት? በሚለው ዙሪያ የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ሊወያዩ ይገባል። ሕዝበ ክርስቲያኑም ራሱን የሚከላከልበት አቅምና አደረጃጀት መፈጠር ሌላኛው አማራጭ ሊሆን ይገባል።

# ''አባትህንና እናትህን አክብር''

(ዘፀ. ፳፥፲፪)

**በእንድርያስ ስንታየሁ**

ልጆች እንደምን ከረማችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን፤ ደኅና:: ዛሬ ይዘንላችሁ የቀረብነው ከዐሥርቱ ትእዛዛት መካከል አንዱ ስለሆነው ትእዛዝ እናትና አባትን ስለማክበር ነው:: ልጆች! እናትና አባትን ማክበር ማለት የወለዱንን ወላጆቻችንን በሚገባ መታዛዝ ነው:: ይህንንም ማድረግ ያለብን ለወላጆቻችን ብቻ ሳይሆን በሥጋ ባይወልዱንም በዕድሜያቸውና በዕውቀታቸው እኛን በጎ ምክር የሚመክሩን ሁሉ እናትና አባቶቻችን በመሆናቸው ለአዛውንቶችም ጭምር ነው::

አንዳንድ ልጆች ግን በየመንገዱ ታላላቆቻቸው፣ አዛውንቶችንና የታመሙትን ሰዎች በማንጓጠጥ እንዲሁም በማሾፍ የሚሳደቡ አሉ፤ ይህ ደግሞ ትልቅ ጥፋት ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ኤልሳዕ የሚባል ደግ ነቢይ ነበር:: የታመሙትን ይፈውሳል፤ የሞተ ሰው ያስነሣል፤ በጣም የተከበረ ሰውም ነበር:: ነገር ግን ሕፃናት ገጹንና አካሉን ሲያዩት ተራ ሰው አድርገው ናቁትና ‹አንተ ራሰ በራ (መላጣ) ውጣ! አንተ ራሰ በራ (መላጣ) ውጣ!› ብለው አፌዙበት:: ልጆቹ ማፌዛቸውን እንደጨዋታ ቆጥረው የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ ሻሩ:: የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕም ዘወርም ብሎ አያቸው፤ በእግዚአብሔር ስምም ረገማቸው፤ ከዱር (ከጫካ) ሁለት ድቦች ወጥተው ከብላቴኖቹ መካከል አርባ ሁለቱን ለሕፃናት ሰባበሩው በሏቸው:: ስለዚህ ልጆች ከኤልሳው ታሪክ እንደምንማረው እግዚአብሔር አምላክ የሚታዘዙትን ቅዱሳን ስለሚወድ እንዲከበሩ እንጂ እንዲናቁ ወይንም እንዲሾፍባቸው አይፈልግም:: (፪ ነገሥት ምዕራፍ ፪ ቁጥር ፳፫)

ልጆች! ጠቢቡ ሰሎሞን ምን ብሏል መሰላችሁ፤ ‹አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ በድቅድቅ ጨለማ ማለትም ሲኦል የሚባል ቦታ ውስጥ ለዘለዓለም ሲቀጣ ይኖራል፤› ይህንን ሁል ጊዜ አስታውሰን አባትና እናታችንን ማክበር አለብን:: ጨለማ እንዳይውጠን መብራት እናበራለን፤ በምሽት በመንገድም ስንሄድ መብራት ከሌለ ጉድጓድ ውስጥ ልንገባ እንችላለን:: መቼም ያለ መብራት መንቀሳቀስ አይቻልም፤ በቀንም ቢሆን ፀሐይ ብርሃን ባይሆነን መንቀሳቀስ ይከብዳልና:: (መጽሐፈ ምሳሌ ፳ ቁጥር ፳)

የሃይማኖት አባቶች ቤታችን መጥተው ጠበል የሚረጩን እና መስቀል የሚያሳልሙን አባቶች በመሆናቸው እነርሱንም ማክበር አለብን:: እንዲሁም በትምህርት ቤት የቀለም ትምህርት በጥሩ ሁኔታ የሚያስተምሩንን፣ ስናጠፋ የሚያርሙን፣ ትልቅ ደረጃ እንድንደርስ በመምከር እና ሳንታዘዝ ስንቀር ቀጥተው የሚያስተካክሉን አባቶች አሉን፤ እነርሱንም ልክ እንደ ወላጆቻችን ማክበርና መታዘዝ አለብን::

ልጆች! በአካባቢያችን የተቸገሩ ወይንም በዕድሜያቸው ያረጁ ሰዎችም እናትና አባቶቻችን ናቸው:: ሱቅ ዕቃ ለመግዛት የሚላካቸው እያጡ የሚቸገሩ ከሆነ ሮጥ ብለን ገዝተን ብናመጣላቸው ይመርቁናል:: እግዚአብሔርም ይባርከናል፤ ይቀድሰናል:: ዓይናቸው የደከመ ሰዎች ማየት ቢከብዳቸው እኛ እጆቻቸውን ይዘን ወደ ቤታቸው ብንወስዳቸው እንዲሁም የተራቡትን ምግብ ብንሰጣቸው እንመረቃለን::

ሌላው ደግሞ ልጆች! አንዳንዴ ከወላጆቻቸው ጋር ሲሄዱ በጣም ደካማ አረጋውያን ሲለምኑ ሲያዩ ‹አባቴ እናቴ! ሳንቲም እርዷቸው ወይንም ሳንቲም እንስጣቸው› በማለት በጎ ነገር እንዲያደርጉላቸው ይለምኗቸዋል:: እነርሱን ለመርዳት ገንዘብ ባይኖራችሁ እንኳን ወላጆቻችሁ እንዲረዱ ማድረግ ይጠበቅባችኋል ማለት ነው፤ እግዚአብሔር የሚወደን ገንዘብ ስላለን ሳይሆን ለሰዎች ስናዝን እና ስንረዳ ነው፤ ይህ ደግሞ ትልቅ ሥራ ነው፤ ልጆች ለዛሬ በዚህ ይቆየን፤ ደኅና ሰንብቱ!

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ትንኝን የምታጠሩ ፥ ግልገልንም የምትውጡ፤

ማቴ . ፳፫፥፳፬

**በረቂቅ መቻል**

የተከበራችሁ አንባብያን መቼም በዕለት ዕለት እንቅስቃሴያችን ልብ ብለን ካስተዋልን የሚደንቁ እና የሚያስገርሙ የሚያስደስቱና የሚያዝናኑ የሚያበሳጩ ነገሮችን በአግራሞት ተመልክተን ወይም ሰምተን ማለፋችን አይቀሬ ነው። አንዳንዴም አስተማሪ የሆኑ ትርኢቶችን ልናይ እንችላለን። እኔም በአንዲት ዕለት ካስተዋልኳቸው ትዝብቶቼ መካከል ለእናንተ ለማካፈል ወደድሁ።

ወሩ ሰኔ ዕለቱ ዐርብ ቀኑ ዐሥራ ሁለት ሰዓቱ ደግሞ በግምት ከዐሥራ ሁለት ተኩል እስከ አንድ ሰዓት ባለው አካባቢ ይሆናል። ቦታው ስድስት ኪሎ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ነው። በዚህ ዕለት ዐይኖቼ ያዩትን በጆሮዬ የሰማሁትን እና በልቤ ያወጣሁ ያወረድሁትን እንዲሁም የተሰማኝን በትዝብት ቅኝቴ ውስጥ ላሳያችሁ ስወድ ከመንፈሳዊ ቅንዓት ተነሥቼ ነው። ለትዝብት ቅኝቴ አትኩሮት እንድሰጥ ምክንያት የሆነኝ በክርስቲያን ወገኖቼ ዘንድ የዕለቱ በዓል ታላቅነት ሰፊ ስፍራ የሚሰጠው በመሆኑ ተከብሮ የሚውለውን የበዓሉን ምንነት በጥቂቱ ለማስታወስ ያህል እግረ መንገዴን ታሪኩን እያወሳሁ የትዝብት ቅኝቴን ልገልጽላችሁ እወድዳለሁ። ወቅቱ ዓለምን እያስጨነቀ ያለው ኮቪድ ፲፱ ወረርሽኝን አስመልክቶ በሚወጡ የመንግሥት አዋጆች እና አተገባበራቸውን ስታዘብ በአብያተ ክርስቲያኖች ላይ አብዝቶ የሚደርሰው አሉታዊ ጫናና ግፍ ከዕለት ዕለት የሚያሳዝንና የሚያበሳጭ ሆኖ ስላየሁት ነው።

በዚህ ቀን ሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ ማልዶ በመነሣት ወደ ቅዱስ ሚካኤል ወዳለበት ቤተ ክርስቲያን ይተማል። ከባድ የሚባል ችግር ካልገጠመው በቀር ሁሉም በሚባል ደረጃ ደጁን ሳይረግጥ ቤተ ክርስቲያንን ሰላም ለኪ ብሎ በሮቿን ስሞ ቅዱስ ሚካኤልን አማልደኝ ርዳኝ ረድኤትህ በረከትህ ይደርብኝ ሳይል የሚውልና ወደ ተሰማራበት የዕለት ሥራ የማይሄድ ክርስቲያን የለም ብል ማጋነን አይሆንም። ከዚህ ጋር ተያይዞ ዐይኖቼ ለሕዝብ ደኅንነት የተመደቡትን የፖሊስ አካላት ብቻ ሳይሆን በበጎ ምግባር ተሰማርተው ቤተክርስቲያንና ሕዝበ ክርስቲያኑን በቅንነትና በማስተዋል ሲያገለግሉ የነበሩትን ወጣቶች በማየት ማድነቅ ጀመርኩ።

ወጣቶቹ እጅ በማስታጠብ፣ አልኮልና ሳኒታይዘር በማቀበል ምእመናን ርቀታቸውን ጠብቀው የዕለቱ የበረከት ተካፋይ እንዲሆኑ ከወዲያ ወዲህ ሲራወጡ ያየኋቸውን የቤተክርስቲያን የቁርጥ ቀን ልጆች ሳላመሰግን እንዳላልፍ ተገደድኩ።

ከእነርሱ በተለየ መልኩ ደግሞ እንጀራ ሆኖባቸው ይሁን ሌላ ተልእኮ ለማስፈጸም ግልጽ ባይሆንልኝም ምእመኑ ባለበት ቆሞ እንኳን መሳለምና ጸሎት ማድረስ ፈልጎ እያለ በዱላ የሚያራውጡትን አይቼ ምናለ ለዛሬ ብዬ ልማጸን ወደድኩ ግን ሰሚ የለም። የሰው ልጆች በትሕትና ራሳቸውን ዝቅ ማድረግ እንደሚገባቸው እና እርስ በእርሳችን መከባበርን ገንዘብ ልናደርጋት የሚያስፈልግ ሲሆን በዚያ በከበረ ዕለት ግን በአንዳንድ የጸጥታ አስከባሪዎች የተመለከትኩት እና የታዘብኩት በዓሉን ለማክበር የመጡ በዕድሜ የገፉ አረጋውያን አባቶችን እና እናቶችን ሳይቀር እየገፈተሩ ለጆሮ የማይመጥን ቃል እየተናገሩ ከፍ ዝቅ አድርጎ በማመናጨቅ ከኢትዮጵያዊነት ባሕል ወግና ልማድ ውጪ

በሆነ መንገድ ቀልባቸውን እየገፈፉ ሲያዳፉዋቸው ማየቱ ልብ ይነካል።

በሁሉም ዘንድ የሚታወቀውና የማይካደው የወቅቱ ችግር የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ መስፋፋት መሆኑ እሙን ነው። ይሁን እንጂ ያን በዓል ምክንያት አድርጎ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት የሚመጣው አማኝ ለቫይረሱ እንዳይጋለጥ ራሱን እንዲጠብቅ መከባበር ባለበት መንገድ ማስተማርና ግንዛቤ እንዲወስዱ በሰለጠነ መንገድ ማድረግ ሲቻል በበሽታው እያመካኙ ለይምሰል ብቻ ነጠላ የለበሰን ክርስቲያን አድኖ ማንገላታቱ ዓላማው ምንድን ነው ብሎ ለመጠየቅ የሚያስችል ድርጊት መሆኑ የትዝብቴ ዋና አትኩሮት ነው።

ሕዝበ ክርስቲያኑ በዚህ ዕለት ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዱ ለራሱና ስለ ሀገር ደኅንነት ለመጸለይ እንጂ ለሌላ ጉዳይ እንዳልሆነ ለማንም ግልጽ ቢሆንም በአንዳንዶች ዘንድ ግን ይህ ያልተዋጠላቸው አካላት ወንጀል እንደ ፈጸመ አስመስለው በአጋጣሚው ተጠቅመው የግል ተልእኮአቸውን ለማስፈጸም መሞከሩ ያስተዛዝባል።

**ራቅ ብለው በብዛት በአንድ አካባቢ ሰብሰብ ብለው ቆመዋል። ምክንያቱም ወደ ቤተ ክርስቲያን በሮች መግባት ቀርቶ ቀረብ ብሎም አማትቦ መሳለም እንዳይችል ተከልክሏል።**

እኔም በዚህች በከበረች እና ለምስጋና በተመረጠች ዕለት እንደ እናት አባቶቼ እንደ እኅት ወንድሞቼ ከበረከቱ ለመሳተፍ ምንም እንኳን ሌሊቱን እንደ አባቶቼ ካህናት በማኅሌቱ ለመሳተፍ ዕድሉን ባላገኝም ኪዳኑን አስደርሼ የጾም ወራት ስለሆነና ቀኑም ዐርብ በመሆኑ ቀሪ የአምልኮ ሥርዓቶችን ተሳትፌ የመልአኩን ረድኤት ለማግኘት ከቤቴ ወጥቻለሁ።

በዚያውም የቃል ኪዳኑ ታቦት ከመንበረ ክብሩ ተነሥቶ በዝማሬና በውዳሴ በዕልልታም ታጅቦ ሲወጣ ተባርኬ ቅዳሴውንም አስቀድሼ በአጠቃላይ በዕለቱ የሚከናወኑትን ምሥጢራት ሁሉ ተሳትፌ በረከቱን ለማግኘት ነጠላዬን መስቀልኛ አጣፍቼ የጸሎት መጽሐፌን ይዤ አንበሳ ግቢ ከሚባለው መስመር የሰማዕታት መታሰቢያ አደባባዩን ልሻገርና በያሬድ ዜማ ወረቡ ወደሚንቆረቆርባት በዓሉን ለማክበር ቅጥሮቿን በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ተውባ ከሩቅ ወደምትጣራው በበዓሉም የአምልኮ የምስጋና ሥርዓት አሸብርቃ ወደምትታየው ቤተ ክርስቲያን ለመግባት ጉዞዬ ሲቃረብ የጸጥታ አስከባሪዎችን በብዛት ሆነው አየሁ።

አደባባይ እንደ መሆኑ ወደ አራቱም ማዕዘን የሚተላለፈውን ሰው በትኩረት ስመለከት ዘርዘር ብለው ቆመዋል። ነጠላቸውን መስቀልኛ የለበሱ ኦርቶዶክሳውያን የአደባባዩን መሻገሪያዎች ሞልተዋቸዋል። ምክንያቱም አደባባዩን ተሻግረው እንዳያልፉና ቀረብ ብለው እንዳይሳለሙ በመደረጋቸው ነው።

ራቅ ብለው በብዛት በአንድ አካባቢ ሰብሰብ ብለው ቆመዋል። ምክንያቱም ወደ ቤተ ክርስቲያን በሮች መግባት ቀርቶ ቀረብ ብሎም አማትቦ መሳለም እንዳይችል ተከልክሏል። እኔም እስኪ ካስገቡኝ ልሞክር ብዬ ወደ ተለያየ ጉዳያቸው ለመድረስ ከሚተላለፉት ሰዎች ጋር አደባባዩን ለመሻገር ስሞክር በእኔ በኩል የነበረው የጸጥታ አስከባሪ ነጠላ መልበሴን እንዳየ አስቆመኝና “ወዴት ነው”? አለኝ እኔም በትሕትና እባክህ ርቀቴን ጠብቄ ወደ ቤተ ክርስቲያን ልግባ ስእለቴንም ላስገባ አልኩት። ይሁን እንጂ በሥርዓት የምለውን እንኳ መስማት አልፈለገም። ከሁኔታው እንደ ተረዳሁት ስእለት ምን እንደ ሆነም የሚያውቅ እንዳልሆነ

ያስታውቃል። በቁጣ ሆኖ ተመለሽ ከዚህ ማለፍ አይቻልም አለኝ።

እኔም ዘወር ዘወር በዬ ዙሪዬን ስመለከት እንደኔ እንዳያልፉ የተከለከሉ ክርስቲያኖች ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ነው። ለተባለው ለወረርሽኙ በሚያጋልጥ ሁኔታ ተፋፍኖ የተሰበሰበው ሰው ብዛቱ ያስደነግጣል። የጸጥታ አስከባሪዎችም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ መከልከላቸውን እንጂ ተከልክለው በሺዎች የሚቆጠሩ ምእመናን በአንድ ላይ መቆማቸውና የነበረውን ትርምስ እያዩ ከምንም አልቆጠሩትም።

**የትራንስፖርት አገልግሎት መሸጫ ስፍራዎች በተለመደው እንቅስቃሴ መሆናቸው በተለይም ጃን ሜዳ በቅርቡ የተቀየረው አትክልት ተራ፣ መነኻሪያዎች ወዘተ በነበረው አይነት እንቅስቃሴ መሆናቸው ግድ ሳይሰጣቸው እንዲሁም በነዚህ ስፍራዎች ለምልክት እንኳ የፖሊስ አባላት የማይታዩ ሆኖ ሳለ የፊት መሸፈኛ አድርጎ፣ አካላዊ ርቀቱን ጠብቆ የቤተ ክርስቲያን ልጆች እጅ የሚታጠቡበትን እና አልኮሎችን በር ላይ አዘጋጅተው በማኖር ከወረርሽኙ ለመጠበቅ እነዚህ ሁሉ በተሟሉባትና ጥንቃቄ በሚደረግባት ቤተ ክርስቲያን ምንም አይነት ሰው ዝር እንዳይል የሚል በሚመስል መልኩያለ የሌለ ኃይል በመጠቀም ክልከላ ማድረግ ምን ታስቦ ነው ያስብላል።**

ያን በውስጤ እየታዘብኩ በዐይነ ኅሊናዬ ሌሎችን ቦታች ሰዎች በብዛት የሚሰበሰቡባቸውን ስፍራዎች መቃኘት ጀመርኩ። የገበያ ስፍራዎች፣ መጠጥ ቤቶች፣ሆቴሎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት መሸጫ ስፍራዎች በተለመደው እንቅስቃሴ መሆናቸው በተለይም ጃን ሜዳ በቅርቡ የተቀየረው አትክልት ተራ፣ መነኻሪያዎች ወዘተ በነበረው አይነት እንቅስቃሴ መሆናቸው ግድ ሳይሰጣቸው እንዲሁም በነዚህ ስፍራዎች ለምልክት እንኳ የፖሊስ አባላት የማይታዩ ሆኖ ሳለ የፊት መሸፈኛ አድርጎ፣ አካላዊ ርቀቱን ጠብቆ የቤተ ክርስቲያን ልጆች እጅ የሚታጠቡበትን እና አልኮሎችን በር ላይ አዘጋጅተው በማኖር ከወረርሽኙ ለመጠበቅ እነዚህ ሁሉ በተሟሉባትና ጥንቃቄ በሚደረግባት ቤተ ክርስቲያን ምንም አይነት ሰው ዝር እንዳይል የሚል በሚመስል መልኩያለ የሌለ ኃይል በመጠቀም ክልከላ ማድረግ ምን ታስቦ ነው ያስብላል።

ወደ ተለያዩ ቦታዎችና ሕዝብ ወደሚበዛባቸው ስፍራዎች ለመሄድ ምንም አይነት ጥያቄ የለም። ለዓለም ጸሎት ወደሚደርስባት ቤተ ክርስቲያን የምትሄድ መስሎ ከታያቸው ግን ወዴት ነው የሚል ጥያቄ ይቀርብልሃል። አንዳንድ አጥቢያዎች ላይ የሚቆሙ የፖሊስ አባላትማ በቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ ቆመህ አማትበህ እንዳትሳለም እንኳ ይከለክሉሃል። የእኔ ትዝብት ያስተዋለው በወረርሽኙ እያመካኙ የቤተ ክርስቲያንን መዘጋት እንደ ስኬት የሚቆጥሩ አካላት መኖራቸውን ነው። የፀጥታ ኃይሎች ማስተዋልና ሕግን በአግባቡ የማስከበር ልምድን ሊተገብሩና ሊያዳብሩ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን የሀገሪቱን ሕግ አክብራ ሥርዓተ አምልኮዋን እንዳትፈጽም መከልከል አግባብነት የለውም። ስለሆነም ሰላምን አስከብራለሁ የሚለው የፀጥታ ኀይል የሃይማኖት ነጻነትን ማክበር ቢችል መልካም ነው።

እግዚአብሔር ልብ እንዲሰጣቸው እየለመንን እኛም ከተኛንበት መንቃት እና ቤተ ክርስቲናችንን መጠበቅ ልባችን ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን ቅጥር እንዳይርቅ መሆን አለበት። እግዚአብሔር የተሻለ ዘመን ያምጣልን የቤተ ክርስቲያንን ጠላቶች ያስታግሥልን።

*አሜን*

# ገና በለጋ ዕድሜዬ እየፈተነኝ ያለ የዝሙት መንፈስ በሽታ እየሆነብኝ ተቸገርኩ

*የተከበራችሁ የስምዐ ጽድቅ ዝግጅት ክፍል እንደምን አላችሁ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ በተሰኘው የዝግጅት ዓምድ ላይ የሚወጡ ምሥጢራዊ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው አስተማሪ ናቸው። በተለይ እንደኔ ደካማ ለሆኑ አቅጣጫ ሰጪና አጽናኝ በመሆናቸው አዘውትሬ እከታተላቸዋለሁ። ታዲያ ከዚህ በፊት ያነበብኳቸው ታሪኮች ብርታት ሆነውኝ እኔም ያለብኝን ውስጣዊ ችግር መፍትሔ ከእናንተ ዘንድ እንደማገኝ ተስፋ አድርጌ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ ወደድኩ።*

*በክርስትና ስሜ ዕጸደ ማርያም እባላለሁ ዕድሜዬ በሃያዎቹ አጋማሽ ውስጥ ነው። የምኖረው እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ሲሆን ገና የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለሁ የዝሙት መንፈስ ተጠናወተኝ። ዕድሜዬ ለአቅመ ሔዋን ከደረሰ ጊዜ አንሥቶ እስከ አሁን በሕልመ ሌሊት እየተገናኘኝ ፈጽሞ ዕረፍት አሳጣኝ። በአሁኑ ሰዓት እንደማንኛውም ሴት ውስጤ የተፈጥሮ ጥያቄ አለ ነገር ግን በጣም ያስጨንቀኛል። በመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞዬ ውስጥ እንደ አቅሜ እርሱን ለመዋጋት እጥራለሁ። የሴትነት ጠባዬ ብዙ አስቸጋሪ አይደለም። ለዓለማዊ ብልጭልጭ ነገሮች ትኩረት አልሰጥም፣ አልባሌ ቦታ ማሳለፍ አልወድም፣ ነፍሴ ዘወትር ለኪዳን ለቅዳሴ ነው የምትፋጠነው ከዚህ መንፈስ ነጻ ለመውጣት በጾም በጸሎት እተጋለሁ፣ ጸበል እጠመቃለሁ መፍትሔ አገኛለሁ በማለት ወደ ቅዱሳት ገዳማት ሁሉ እየሄኩ የቅዱሳኑን ተራዳኢነት ደጅ እጠናለሁ። ይባስብሎ አሁን አሁን ተስፋ እንድቆርጥ እያደረገኝ ጾም ጸሎቴን እንዳላደርግ ሕመም እየሆነብኝ ተቸገርኩ ታዲያ ከዚህ ችግር እንዴት መውጣት እችላለሁ? እባካችሁ ከችግሬ መውጣት የምችልባቸውን መፍትሔዎች አመላክቱኝ*

ውድ እኅታችን ዕጸደ ማርያም በቅድሚያ ለችግርሽ መፍትሔ ከኛ ዘንድ መሻትሽና ላጋጠመሽ ፈተና በግልጽ ስላማከርሽን ልባዊ ምስጋናችን የላቀ ነው። በመቀጠል አሁን እያጋጠመሽ ያለውን የዲያብሎስ ውጊያና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በሚከተለው መልኩ ለማየት እንሞክራለን።

ስለሆነም እኅታችን ዕጸደ ማርያም በአንቺ ሕይወት ውስጥ በቀጥታ ላጋጠመሽ ችግር ምላሽ ከመስጠታችን በፊት ከገለጽሽልን ታሪክ ለመረዳት በቻልነው መጠን እነዚህን ያጋጠሙሽ ዋና ዋና ችግሮች መሠረታዊ ምክንያቶቹንና የመፍትሔ ሐሳቦች ምን መሆን አለባቸው የሚለውን እንመለከታልን።

ውድ እኅታችን ዕጸደ ማርያም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ" በማለት እንደነገረን ከሁሉ አስቀድመን በዓለም ስንኖር ፈተና መኖሩን እንዲህ መባሉን እንድትገነዘቢ እንወዳለን። (ዮሐ. ፲፮፥፴፫)

ወደ ዐቢይ ጉዳያችን ከመግባታችን በፊት አንቺም ከዚህ በፊት የነበረሽን መንፈሳዊ ጥንካሬ እና በጎ መንገድ ለራስሽ አጉልተሽ እንድታዪ ምክራችን ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ በአንቺ ታሪክ ሌሎች ምእመናንም ይማሩበት ዘንድ ለጥያቄሽ መልስ ይሆናል ብለን ያመንበትን ነገር እንደሚከተለው አቅርበነዋል መልካም ንባብ።

አስቀድሞ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዞዋችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ” ብሎ ያስተማረን ፈተና በሁላችን ሕይወት እንደሚመጣ ሲያጠይቅ ነው:: (ዮሐ. ፲፮፥፴፫ ፣ማቴ ፬፥፩) ፈታኝ የሆነው ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ጌታን ሳይቀር በትዕቢት ፣ በስስት እና በፍቅረ ንዋይ ፈትኖት ነበር:: ነገር ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትዕቢትን በትሕትና፣ ስስትን በትዕግሥት፣ ፍቅረ ንዋይን በጸሊዐ ንዋይ፣ ድል ነሥቶ በተግባር አርአያ ሆኖናል:: ፈታኝ ዲያብሎስ በመጀመሪያ ራሱ ተፈትኖ የወደቀ ቢሆንም የሰውን ልጅ መፈተን ጥንትም ልማዱ ነው:: አዳምና ሔዋንን ፈትኖ ያሳተው፣ ኢዮብን በሀብቱ ጥፋት በልጆቹ ሞትና በጤና ማሳጣት የፈተነው፣ የበርካታ ቅዱሳንን ሕይወት ሁሉ ሲፈትን የኖረው፣ ዛሬም የክርስቶስ የሆኑትን የሚፈትነው፣ እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንም በየዘመናቱ በልዩ ልዩ ሰዎች እያደረ የሚፈትናት ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ነው::

እኅታችን ዛሬ በፈተና ውስጥ መሆንሽ እምነትሽ ይፈተን ዘንድ መሆኑን ልትረጂ ይገባል :: ፈተና ወደ ሁላችን ሕይወት ይመጣ ዘንድ ግድ ስለሆነ ትኩረትሽ ፈተናው ላይ ሳይሆን መፍትሔው ላይ መሆን አለበት:: በክርስቶስ የምናምን ክርስቲያኖች ሁላችን በልዩ ልዩ መንገድ እንፈተናለን:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈተና እንዳለብን ብቻ ሳይሆን ፈተናውን በምን ድል ማድረግ እንደምንችልም አሳይቶናል:: “ስለዚህም በክፉ ቀን መቃወም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ጋሻ ያዙ፤እንድትጸኑም በሁሉ የተዘጋጃችሁ ሁኑ” የእግዚአብሔር ጋሻ የተባለው ጾም፣ ጸሎት እና ስግደት ነው:: እነዚህን ወደኋላ ወደፊት ሳንል በሥርዓቱ በመፈጸም ጠላት ዲያብሎስን ድል ልንነሣው እንችላለን:: (ኤፌ ፮፥፲፫)

እህታችን በመጀመሪያ ለግንዛቤ ይሆንሽ ዘንድ የህልመ ሌሊት ምንነትንና ወደ ሰው ልጆች በምን አይነት ሁኔታ እንዴት እንደሚገባ ለማንሣት እንወዳለን::

## ሀ/ የሕልመ ሌሊት (nocturnal emission)

ሕልመ ሌሊት በጥልቅ እንቅልፍ ላይ ሳሉ ወንዶችን ሴት ሴቶችን ደግሞ ወንድ ተመስሎ በመቅረብ በገሃድ ፈቃደ ሥጋ የሚፈጽሙ እያስመሰለ ዘራቸውን እንዲያፈሱ የሚያደርግ በሥነ ልቡና ና መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር ችግር ነው:: የሚከሠትባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር ስንመለከት ደግሞ

### ፩. በሥነ ሕይወታዊ ምክንያት (biological cause)

ለአቅመ አዳምና ለዐቅመ ሔዋን የደረሱ ወጣቶች ዘር የሚወጣቸው በልዩ ልዩ መንገድ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ግን ተኝተው ሳለ በጠለቀ እንቅልፍ ሆነው ሕልም በሚያልሙበት ወቅት ነው:: ይህ ሲሆን እንደ ጤናማ የተፈጥሮ ሂደት ይቆጠራል:: አንዳንድ ጊዜ አብዝቶ ከልክ በላይ ከመመገብ የተነሣ ሕልመ ሌሊት ሊያጋጥም ይችላል :: ከዚህ በተለየ በሴት እኅቶቻችን ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፈሳሾች ሁሉ ሕልመ ሌሊት ናቸው ማለት አይቻልም ምናልባት ከአካላዊ ጤና ጋር የተያያዘ ችግር ሊሆን ይችላል::

### ፪. በሥነ ልቦናዊ ምክንያት (psychological) ስጋትና ጭንቀት (anxiety and stress)

በተደጋሚ ሕልመ ሌሊት የሚያጋጥማቸው እኅቶችና ወንድሞች ወደ መኝታ መሔዳቸውን ሲያስቡ ሕልመ ሌሊት ያገኘኝ ይሆን ብለው ይሰጋሉ ፤ ይጨነቃሉ፤ ከዚህም የተነሻ የሥነ ልቡና ጫና ውስጥ ይገባሉ:: ይህ የሥነ ልቡና ጫናም ለሕልመ ሌሊት ሊያጋልጣቸው ይችላል:: ይህም እንዳይሆን ከመኝታ በፊት አዕምሮን ነጻ የሚያደርጉ መንፈሳዊ መዝሙሮችን ማድመጥ መጻሕፍትን ማንበብ ይመከራል::

### ፫. ክፉ ሐሳብ (bad thought)

በቀን ውሎአችን የተቃራኒ ጾታ ግንኙነቶችን በማሰላሰል ስንውል:: በተለይ የዝሙት ስሜት የሚቀሰቅሱ ሁኔታዎች ማንበብ ማየትና መስማት በቀላሉ ለሕልመ ሌሊት

ሊያገልጡ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ የሠሩትን ርኩሰት እንዲህ ሆኜ እንዲህ አድርጌ እያሉ ለአቻ እኩዮቻቸው በመንገር አንተስ፣ አንቺስ በዚህ የወጣትነት ዕድሜህ ለምን ትታሠራለህ? ለምን አትደሰቺም? በሚለው የአቻ ግፊት በመማረክ በግብር ባይፈጽሙ እንኳን አዕምሮአቸው የሩካቤ ሥጋ ሐሳብን ሲያሰላስል ሲውል በመኝታ ጊዜ ሕልመ ሌሊት በቀላሉ ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡

ለመዝናናት ብለን የምንመለከታው ፊልሞች፣ የምናነባቸው ጽሑፎች የዝሙትን ስሜትን የሚቀሰቅሱ ከሆኑ በተለይም ወሲባዊ ግንኙነትን በግልጽ የሚያሳዩ ምስሎችን የያዙ ከሆኑ በቀላሉ ሕልመ ሌሊት እንዲያጋጥመን ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### ፬. በአጋንንት ፈተና ምክንያት

አጋንንት የሰውን ልጅ በተኛበት ክፉ ክፉ ሕልም በማሳየት ይፈትኑታል፡፡ ሕልመ ሌሊት በራሱ ኃጢአት አይደለም አንድ ሰው በንቁ ልቡና ሳለ ወደ ኃጢአት የሚመሩትን ነገሮች ተግቶ እየተቃወመ ነገር ግን በተኛና ባንቀላፋ ጊዜ ሕልመ ሌሊት ቢያገኘው ሕልሙ ዕዳ ሆኖ አይቆጠርበትም፡፡

ነገር ግን ሕልመ ሌሊት ያጋጠመው ሰው በነቃ ጊዜ ድርጊቱን ካልተቃወመ ካልተጸጸተ ደስ ከተሰኘበት በተግባር እንደፈጸመው ኃጢአት ሆኖ ይቆጠርበታል፡፡ ምክንያቱም ከምኞት ብዛትም ሕልመ ሌሊት ሊከሠት ይችላል፡፡ ነፍስ በሕልም ምክንያት ከተጠያቂነት ነፃ መሆን የምትችለው ሥጋ ከእንቅልፍ ውጭ በሚሆንበት ጊዜ ተግባረ ዝሙትን በመቃወምና በመጥላት ከእግዚአብሔር ጋር መሆኗን ስታስመሰክር ብቻ ነው፡፡

## ለ. ለችግርሽ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ምክሮች

ውድ እኅታችን ለችግርሽ መፍትሔ ሊሆኑ ይችላሉ ብለን ያመንባቸውን የሚከተሉትን ምክሮች እንጠቁምሻለን፡-

### ፩. እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ

አባታችን ክቡር ዳዊት «አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም፤ በከንቱ የሚገበዙ ያፍራሉ፡፡» መዝ. ፳፭፥፫ እንዳለን የማያሳፍረውን እግዚአብሔርን ተስፋ አድርገሽ የእርሱን ምሕረት በመጠበቅ ጽኚ፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረውን ስለማይረሣ እኛም ልጆቹ በተስፋ ስለምንኖር "አቤቱ፥ መንገድህን አመልክተኝ፥ ፍለጋህንም አስተምረኝ አንተ የመድኃኒቴ አምላክ ነህና በእውነትህ ምራኝ፥ አስተምረኝም፤ ቀኑን ሁሉ አንተን ተስፋ አድርጌአለሁ፡፡"(መዝ. ፳፭፥፬ ) እያልሽ በእግዚአብሔር የማዳን ተስፋሽን በጸሎት ልትተጊ ይገባል፡፡

ምናልባት ለችግርሽ ፈጣን ምላሽ ከመሻት የተነሣ እግዚአብሔርን በተስፋ ስትጠብቂ የዘገየ እየመሰለሽ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ሊሰማሽ ይችላል፡፡ ዲያብሎስ በእምነት ጸንተን ከእግዚአብሔር የምንቀበለውን ጸጋ ስለሚያውቅ ተስፋ እንድንቆርጥ ሊያደርገን ይችላል፡፡ ስለዚህ ልትነቂ ያስፈልጋል ይልቅስ የእግዚአብሔርን ፍቅሩን ልታስቢ አኅደለብኝ ከምትዪው ነገር ይልቅ ያደረገልሽን መልካም ነገር እያሰብሽ ክፉን ሐሳብ ልትቃወሚ ይገባል፡፡

### ፪. መንፈሳዊ ትጋትን ማጠናከር

መንፈሳዊነት በጊዜ ፣በቦታና በሁኔታ የሚገደብ ሳይሆን ዘወትር በየትኛውም ቦታ በየትኛውም ሁኔታ በማግኘት በማጣት ፣ በመውደቅ በመነሣት ፣በኃዘን በደስታና በፈተና በድል ውስጥም ሊታይ ሊገለጥ ይገባል፡፡ የመንፈሳዊነት አንደኛው ጥቅም በሕይወታችን መከራ ወይም ፈተና ሲመጣ ድል የምናደርግበትን መንገድ የሚያሳየን መሆኑ ነው፡፡

አንዳንዶች የጥቂት ጊዜ ፈተናን መታገሥ እየተሳናቸው ከመንፈሳዊነት ሲንሸራተቱ ባስ ሲልም ከሃይማኖት ሲጎድሉ እንመለከታለን፡፡ ነገር ግን ኦርቶዶክሳዊ መንፈሳዊነት ከንግግር በላይ በፈተና ጸንቶ መገኘትን ይጠይቃል፡፡

### ፫. በፈተና መጽናት

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው» (ያዕ . ፩፥፲፪) እንዳለ በፈተና ልንጸና ይገባል፡፡ይኼንንም በብዙ ቅዱሳን ሕይወት ውስጥ የምንመለከተው ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እስከ መጨረሻው ድረስ ጸኑ የጸኑ ቅዱሳን አባቶች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጻድቁ ኢዮብን ምሳሌ አድርገን ማንሣት እንችላለን፡፡ ጻድቁ ኢዮብ ሀብት ንብረቱን፣ አሥር ልጆቹን በአንድ ቀን ውስጥ ያጣ መላ ሰውነቱም በቁስል ተመትቶ በመከራ ውስጥ የነበረ ሰው ነበር፡፡ ኢዮብ ግን ሀብቱን ልጆቹንና ጤናውን አጥቶ ሳለ እግዚአብሔርን ባረከ «. . . እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔርም ነሣ፤የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን፡፡» (ኢዮ. ፩፥፳፩) ከእርሱ ታሪክ ጽናቱን አሳይቶናል፡፡

## ፬. የራስሽን ድርሻ ማወቅና መወጣት

የተከበርሽ እኅታችን ለገጠመሽ ፈተና የመጀመሪያው መፍትሔ ራስሽ ጋር ሊሆን ስለሚችል አስቀድመሽ ራስሽን ከእኔ የሚጎድለው ምንድነው ብለሽ ልትጠይቂ ያስፈልጋል፡፡ በእርግጥ በእግዚአብሔር ተራዳኢነት አምናለሁ ወይ? ጾም ጸሎቱ እንደሚገባ ነው ወይ? በንስሐ ወደ ከእግዚአብሔር ተመልሻለሁ ወይ? የምመካው በእግዚአብሔር ነው ወይስ በመንፈሳዊ ሕይወቴ በምደክመው ድካም? ብለሽ ራስሽን ልትጠይቂ ራስሽን ልትመረምሪ ይገባል፡፡

## ፭. ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ

ሌላው መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ዘወትር ቃለ እግዚአብሔርን በማንበብ በኅሊናችን ሊፈትኑን ከሚችሉ ክፉ ሐሳቦች መከልከል ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ በቃሉ እንድትጽናኚ፣ በእግዚአብሔር ጠባቂነት እንድታምኚ እንድትጸኚ ዲያብሎስን መቃወም እንድትችዪ ስለሚያደርጉሽ ማታ ወደ መኝታ ከመሄድሽ በፊት ቅዱሳት መጻሕፍትን ዘወትር ልታነብቢ ይገባል፡፡ "ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል፡፡" ተብሎ እንደተጻፈ ሰይጣን ከእኛ ይርቃል (ያዕ . ፬፥፯—፰፣ማር. ፯፥፳—፳፫)

## ፮.ተስፋ አለመቁረጥ

ከሁሉ በላይ እስከ ዛሬ እግዚአብሔር በፈተና ውስጥ አብሮሽ እንደነበር አሁንም ቢሆን አብሮሽ እንደሆነ ልትረጂ ይገባል፡፡ ነገር ግን በእንዲህ ዓይነቱ ውጊያ ዲያብሎስ የእግዚአብሔር ጥበቃ ከአንቺ የራቀ በማስመሰል ተስፋ እንድትቆርጪ ለማድረግ ይጥራል፡፡ አልፎ ተርፎ ለመንፈስ ዝለት ከቤተክርስቲያን በማራቅ በእግዚአብሔር ላይ ያለ መተማመን በማሳጣት በታላቅ ሥነ ልቡናዊ ውድቀት ላይ ይጥልሻል፡፡ ነገር ግን ዘወትር በፈተናሽ ውስጥ እግዚአብሔር አብሮሽ እንዳለ በማመን ተስፋ ባለመቁረጥ በመንፈሳዊ ሕይወትሽ ልትጸኚ ወደ እግዚአብሔር መቅረብሽን ልትቀጥዪ ይገባል፡፡ "እግዚአብሔር መልካም ነው በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነውና፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት "እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ በርታ ልብህ ይጽና" ብሎ እንደተናገረው የእግዚአብሔርን ቸርነት በተስፋ ጸንተሽ ልትጠባበቂ ይገባል፡፡ (ናሆ. ፩፥፯፣መዝ ፳፯፥፲፬)

## ፯. መጾም

ጾም መድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ ናትና ጾምን ከመጾም ልትዘገዪ አይገባም፡፡ በሰውነት ላይ የዝሙት ጾር ጸንቶ ሳለ አለመጾም አብዝቶ መመገብ ከእሳት ላይ ነዳጅ እንደ መጨመር ነው፡፡ " አብዝቶ መመገብ ከወጣትነት ጋር የኃጢአት ሐሳብን በግድ እንዲመጣ ያደርጋል" ፡፡ በዝሙት ሥራና ሐሳብ በእጅጉ የሚፈተኑ ሰዎች በሚገባ መጾም አለባቸው፡፡ ስለዚህ ጾም ርኩሳን መናፍስትን የኃጢአት ሐሳብን ለመቃወም ለማራቅ ስለሚጠቅም በሚገባ ልትጾሚ ያስፈልጋል፡፡ (ማር ይስሐቅ አንቀጽ ፳፥፩)

## ፰. ጸሎት አለማቋረጥ

በክርስቶስ ሐዲስ ሕይወት ስለመኖሩ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይነግረናል "ሰውነታችሁን ለእግዚአብሔር ሕያውና ቅዱስ ፥ ደስ የሚያሰኝም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እማልዳችኋለሁ፡፡" (ሮሜ ፲፪፥፩ )፡፡ ስለዚህ መቼም ቢሆን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ በመገዛት በተስፋ ጸሎት ማድረግ ይገባል፡፡ ሕልመ ሌሊት ያገኘሽ ጊዜ በዕለቱ በቤትሽ ጸልዪ በነጋታው ልብስሽን ካጠበሽ ወይም ከቀየርሽ ገላሽን ከታጠብሽ በኋላ አካላዊ ና መንፈሳዊ ንጽሕናሽን በመጠበቅ ራስሽን ሐዲስ አድርገሽ ወደ ቤተክርስቲያን

መግባት ትችያለሽ ወደ ቤተ ክርስቲያን ባትገቢም በጸሎት በትምህርትና በመሳሰሉትን መንፈሳዊ ተግባራት ላይ በበጎ ተግባሮች መሳተፍ ትችያለሽ። ስለሆነም ይህንን ሳታቋርጪ ለማድረግ መበርታት ይኖርብሻል። “ለሥራ ከመትጋት አትስነፉ፤ በመንፈስ ሕያዋን ሁኑ፤ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ታገሡ ለጸሎት ትጉ።” (ሮሜ ፲፪፥፲፩-፲፪) እንደተባለው

**በገዳም ያሉ መናንያን አባቶቻችን ከጾም ከጸሎት ከመንፈሳዊ አገልግሎት በተጨማሪ ራሳቸውን በተግባረ ዕድ በእርሻ ሥራ ይጠምዳሉ።**

### ፱. ራስን በሥራ መጥመድ

በገዳም ያሉ መናንያን አባቶቻችን ከጾም ከጸሎት ከመንፈሳዊ አገልግሎት በተጨማሪ ራሳቸውን በተግባረ ዕድ በእርሻ ሥራ ይጠምዳሉ። ይህን የሚያደርጉት የዚህን ዓለም ሀብት ንብረት ለማከማቸት ሳይሆን ለቁመተ ሥጋ የሚሆናቸውን የዕለት ምግብ ለማግኘትና ሥራ ከመፍታት የተነሣ የኃጢአት ሐሳብ ኅሊናቸውን እንዳያሳድፍባቸው ነው። ለዚህም ነው ሥራ የፈታ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል የሚባለው ጸሎቱን ፈጽሞ ተግባረ ዕድ ቢጠፋ እንኳዋን ኅሊናው በዓለም ሐሳብ እንዳይጠመድ ለራሱ ሥራ ፈጥሮ ራሱን በሥራ ይጠምዳል ማለት ነው። ስለዚህ አንቺም በዚህ ክፉ ሐሳብ እንዳትጠመጂ ራስሽን በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ተግባራት ልትጠምጂ ይገባል።

ውድ እኅታችን የእስከ ዛሬው ትጋትሽና ጽናትሽ በእርግጥም እግዚአብሔር እንዳልተለየሽ የሚያመላክት ሲሆን አሁንም የበለጠ እንድትተጊ እንድትጸኚ እያልን ምናልባት ጽሑፋችንን ስናጠቃልል ሕልመ ሌሊት በጥልቅ እንቅልፍ ላይ ሳሉ ወንዶችና ሴቶች ዘራቸውን እንዲያፈሱ የሚያደርግ የሥነ ልቦና ና የመንፈሳዊ ሕይወት ችግር ነው። ሕልመ ሌሊት በራሱ ኃጢአት እንዳልሆነ ነገር ግን ሲያጋጥም በግብሩን መደሰት ግን ኃጢአት እንደሆነ ይልቅስ ግብሩ መጥላት መቃወም እንደሚያስፈልግ ተመልክተናል። በእኅታችን ታሪክ ውስጥ በፈተና የመጽናትን አስፈላጊነት፣ መንፈሳዊ ትጋትን ከጊዜ ከሁኔታ በላይ ሊገለጥ እንደሚገባ፣ ለዚህም መጽናት እንደሚያስፈልግ ፣ ለመጽናት ተስፋ ባለመቁረጥ እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ እንደሚያስፈላግ ተመልክተናል።

እኅታችንም ከእግዚአብሔር ፈጣን ምላሽ ከመሻትሽ የተነሣ እግዚአብሔርን በተስፋ ስትጠብቂ የዘገየ እየመሰለሽ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ሊሰማሽ ስለሚችል ፈተናውን በትዕግሥት ማሰላሰል ይኖርብሻል። የእግዚአብሔርን ፍቅሩን ልታስቢ አጎደለብኝ ከምትይው ነገር ይልቅ ያደረገልሽን መልካም ነገር እያሰብሽ ክፉውን ሐሳብ ልትቃወሚ ይገባል።

በመጨረሻም ለአጋጠመሽ ችግር መፍትሔው አስቀድመሽ እንደእግዚአብሔር ቃል ራስሽን ልትጠይቂ ልትመረምሪ የሚገባ ሲሆን ከዚህ ባለፈ ዘወትር ቃለ እግዚአብሔርን በማንበብ፣በመጾምና በመጸለይ በክፉ ሐሳብ እንዳትጠመጂ ራስሽን በሥራ ልትጠምጂና ተስፋ ባለመቁረጥ በጽናት ማዳኑን ምሕረቱን በተስፋ ልትጠባበቂ ይገባል። ብዙ ጊዜ በመንፈሳዊ አቅማችን የጠነከርን ይመስለንና ዲያቢሎስን እንዳሸነፍነው በማሰብ መልሰን በመንፈሳዊ ሕይወታችንና በአገልግሎት ዝለን ዳግም በመውደቅ በሥውር የዲያቢሎስ ወጥመድ ላይ እንወድቃለን። ወደ ቤተ እግዚአብሔር ዝም ብለን በልምምድ እንመላለሳለን ስለዚህ የምታደርጊውን ሁሉ በጥበብ በማስተዋል መሆኑን ለመገንዘብ ሞክሪ። ከዚህ በተጨማሪ ምናልባትም ሰይጣን አንቺ መንፈሳዊ ትጋትሽን ባጠነከርሽ ቁጥር እርሱም የማጥፊያ ጥበቡ ስለሚረቅና ኃይሉን ጨምሮ ዘወትር አንቺን ለመጉዳት ስለሚተጋ እንደ ቅድስት አፎምያና እንደ ሌሎች ቅዱሳት አንስት የዳኑትን በማንበብና ጽኑ ተጋድሎን በመጋደል ከእግዚአብሔር በትዕግሥት የሚገኘውን ፍሬ ንቁሕና ብልህ ሴት ሆነሽ እንድትጠብቂ ልንመክርሽ እንወዳለን።